# የቀብርና ሀዘን ሥርዓት ክዋኔዎች በወሊሶ ሊበን ኦሮሞ[1]

ደሰታ አማረ

## አጠቃሎ

*ይህ ጥናት በወሊሶ ሊበን ኦሮሞ የቀብርና የሀዘን ሥርዓት ላይ ያተኩራል። በጥናቱ አካባቢ ሞት ከተከሰተበት ሰዓት ጀምሮ እስከ ሀዘኑ ፍፃሜ በባህሉ በተዋቀሩ ማህበራዊ ተቋሞች የሚከወኑ ሥነርዓቶች አሉ። የእነዚህ በቅድመ ቀብር፣ በቀብርና ድህረቀብር የሚከወኑ ሥርዓቶችን የሚያሳዩ መረጃዎች የተሰበሰቡት በቃለመጠይቅና በምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ሲሆኑ መረጃዎቹ ከህይወት ዑደት የደረጃ ሽግግር አንፃር ተንትነዋል። በትንተናውም ሞተው በሚለዩና ወደ "አያት ቅድመአያቶቻቸው በሚደመሩ" ወገኖች ሰበብ ህዝቡ ተሰባስቦ የሚከውናቸው ድርጊቶች አብሮነቱን፣ መተጋገዙንና ፍቅሩን እንደሚያድስ ባህላዊ እሴቶቹን እንደሚጠብቅ አጉልተው የሚያሳዩ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል።*

## መግቢያ

ወሊሶ ኦሮሞ ከሊበን መጫ ሶስት ልጆች ታላቅ ተብሎ የሚታወቀው ነው፡፡ እነዚህ የሊበን ልጆች ተብለው የሚጠሩ ወሊሶ፣ አመያ እና ኩታዬ ንዑሳን ጎሣዎች በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች የሚኖሩ ናቸው፡፡ ይህ ጥናት ያተኮረው በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን በወሊሶ፣ ዳዎና ወንጪ ወረዳዎች በሚገኙት የቀብርና የለቅሶ ሥርዓት ላይ ነው ፡፡

## የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ሞት የሰው ልጅ ሁሉ የሚጋፈጠው እና ዋና ዋና ከሚባሉ የህይወት ዑደቶች (እንደ ወሊድና ጋብቻ ሁሉ) አንዱ ሲሆን፣ በክስተቱ የሰዎች የርስበርስ ግንኙነት በግልፅ የሚታይበት፣ የተለያዩ የፎክሎር ዘውጎች (genres) በተፈጥሮአዊ አውዳቸው የሚከወኑበት ነው። የርዕሱም መመረጥ በዚህ የህይወት እርከን እነዚህን ህያው ሆነው የማህበራዊ (መንፈሳዊና ዓለማዊ) ህይወት ገላጭ የሆኑ የፎክሎር ዘሮችና ክዋኔያቸውን ለመተንተን ነው፡፡

[1] ይህ ጥናት "የሕይወት ዑደት( ወሊድ፣ጋብቻ፣ሞት)ሥርዓቶች ክዋኔ ትንተና በወሊሶ ሊበን ኦሮሞ" በሚል ርዕስ በ2007 ዓ.ም የሰራሁት የፒኤችዲ ጥናት አንድ ምዕራፍ ላይ ያተከረ ሲሆን መረጃዎቹ ከዚያ ወዲህ ከጥናቱ አካባቢ በተገኙ መረጃዎች ዳብረው ቀርበዋል።

**የጥናቱ ዓላማ**

የወሊሶ ሊበን ኦሮሞ ማንነትና አተያይ ማሳያ ከሆኑት የባህሉ ዘርፎች መካከል በለቅሶ ሥርዓት ምክንያት ከሚፈጠሩ( ከሚገለጡ) የፎክሎር ዘውጎች፣ ተምሳሌቶች እና ከሚሰጡት ፋይዳና የሕዝቡ ተሳትፎ አንፃር በመግለፅና በመተንተን ከክዋኔው በስተጀርባ ያለውን የማህበረሰብ ዕውቀት ማሳየት ነው፡፡

**የጥናቱ መረጃ አሰባሰብና አተናተን ዘዴ**

በሞት ሥርዓት ክዋኔዎች ላይ የሚሳተፈው ህዝብ የርስበርስ ግንኙነትና በየክዋኔዎቹ የሚፈጠሩ የፎክሎር ዘውጎች ምን ምን እንደሆኑ ለመለየት ቃለመጠይቅ፣ ምልከታና ተሳትፎአዊ ምልከታ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በክዋኔው መገኛው ቋንቋ "አፋን ኦሮሞ" ሲሆን አፍ የፈታሁት በቋንቋው በመሆኑ አስተርጓሚ አላስፈለገም፡፡ እነዚህ የተሰበሰቡት መረጃዎችም ከህይወት ዑደት ደረጃዎች አከዋወንና ገለፃዊ ትንተና አንፃር ተመርምረዋል፤ ተተንትነዋል።

**የፅንሰ ሀሳብና ንድፈ ሀሳብ ማዕቀፍ**

ሥርዓት ወይም የዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ የሆነው የህይወት ዑደት ከፎክሎር የጥናት ዘርፎች(sub genres) አንዱ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ፎክሎር የህዝቦችን ልማዶች፣ ወጎች፣ እምነቶችና ህዝባዊ ጥበቦችን ያካተተ ሰፊ የባህል አካል ነው፡፡ ይህንን የባህል አካል Dorson (1972፡2-4) በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍሏል ።(1) ሥነቃል (2) ቁሳዊ ባህል (3) ማህበራዊ ልማድ እና (4) ማህበረሰባዊ ትውን ጥበባት ናቸው። በዚህ ክፍፍል መሠረት የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ሥርዓት በማህበራዊ ልማድ የፎክሎር ክፍል ውስጥ ይካተታል።

ማህበራዊ ልማድ ሰፊ ነው፡፡ በርካታ ንዑሳን የፎክሎር ዓይነቶችን ያካትታል፡፡ ዋናው መገለጫው የህዝቦች ወይም የቡድኖች ማህበራዊ የእርስበርስ ግንኙነቶች የሚጎሉበት፣ በጋራ የሚከወኑና የሚደጋገሙ ጉዳዮች ማጠንጠኛ መሆኑ ነው፡፡ ማህበራዊ ልማድ በውስጡ በዋናነት የተለያዩ በከበራ የታጀቡ ሥርዓቶች (Rituals) እንደ ወሊድ፣ ጋብቻ እና ሞት የመሳሰሉትን ያቅፋል፡፡

በዚህ መጣጥፍ ውስጥ ሥርዓት የሚለውን ቃል፣ ለ "Ritual" የእንግሊዘኛ ቃል ትርጉም ተደርጎ የተወሰደው ሌላ አቻ የሆነ አማርኛ ፍች የሚሰጥ መረጃ ስላልተገኘ በመጠኑ ተቀራራቢ መስሎ የታየው "ምርጥ እንግሊዝኛ አማርኛ መዝገበ ቃለት" በሚለው መጽሐፍ ውስጥ "Ritual - የበዓል ሥርዓቶች" ተብሎ የተበየነው ነው ፡፡ በአማርኛ ቋንቋ የጋብቻ ሥርዓት፣ የቀብር ሥርዓት የሚሉ አገላለፆች ለፍችው ተቀራራቢነት ይኖረዋል በሚል ተወስዷል፡፡

ሥርዓቶች በተደጋጋሚ የሚከውኑ፣ በክፍል በክፍል የሚቀርቡ መነሻ መድረሻ ያላቸው፣ ተምሳሌት የተላበሱ የከበራ ድርጊቶች ናቸው፡፡ በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ የሚከበሩ

መንፈሳዊና ዓላማዊ በዓላት እና የተለያዩ ሌሎች በከበራ መልክ የሚዘጋጁ ክዋኔዎች በሥርዓቶች (Ritual) ውስጥ ይታቀፋሉ (Sims and Stephens, 2005:95) ፡፡

ሥርዓቶች እንደ Van Gennep (1960) አገላለፅ በሁለት ዋናዋና ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡ አንደኛው አንድ ሰው በህይወት ዘመኑ ከአንድ ማህበራዊ ደረጃ ወደ ሌላ ማህበራዊ ደረጃ የሚሸጋገርበትን ለምሳሌ በወሊድ፣ በጋብቻ፣ በሞት ጊዜ የሚከወኑትን የሚይዝ ሲሆን፣ ሁለተኛው በጊዜ (ወቅቶች) መቀያየር የሚከሰቱ ለውጦች፣ የአዲስ ዓመት፣ የአዲስ ጨረቃ ወቅታዊ ክስተቶችን ምክንያት በማድረግ የሚከወኑ ከበራዎችን የያዘ ነው ፡፡

ከሁለቱ ክፍሎች የዚህ ጽሑፍ ትኩረት ከህይወት ዑደት ሥርዓቶች በሞት ላይ በመሆኑ ስለሞት አጠቃላይ የሆኑ ፅንሰ ሀሰቦች ተያይዘ ቀርበዋል። በመጀመሪያ ሞት ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያስፈልጋል። ከመዝገበ ቃላት ፍች ብንነሳ፣ የተለያዩ መዝገበ-ቃላት ለሞት በተለያየ መንገድ ፍች ይሰጣሉ። ለምሳሌ በዌብስተር የእንግሊዝኛ መዝገበ-ቃላት ሞት የሚለውን ቃል፡- ማለፍ፣ የህይወት መጨረሻ ወይም የአንድ ነገር ተበላሽቶ ወይም ጠፍቶ መቅረት በማለት ይፈተዋል።

የጤና ባለሙያዎች ከሙያቸው አንፃር በየጤና መዝገበ ቃላት "ሞት የህይወት መጨረሻ ነው ፤ የሰው ልጅ ዋና ዋና የአካል ሥራ (ተግባር) ሙሉ በሙሉ መቆም ፡-የልብ ምት ሲቆም፣ እስትንፋስ ሲጠፋና አእምሮ ሥራ ሲያቆም ሞተ ይባላል፡፡" (www.rationalskepticim.org...June 21, 2013 9:50) በማለት ይበይኗል፡፡

ከባህልና ሃይማኖት አንፃር ሲታይ ደግሞ ሞት መገለጫው ይለያል። በተለይ ከምዕራባዊያን ባህል ውጭ የሆኑ ህዝቦች በሃይማኖታቸው፣ በአተያያቸው፣ በሥርዓት ክዋኔዎቻቸው እና በአንዳንድ ማህበራዊ ተቋሞቻቸው አማካይነት ሞትን ምንም እንዳልሆነ አድርገው አቅልለው ህዝቦች እንዲቀበሉት ያደርጋሉ። እንዲህ ዓይነቶቹ ባህሎች ሞትን ዘላለማዊ መለየት አድርገው አይመለከቱም። ህይወት በሌላ መልኩ ቀጥሏል ብለው ያምናሉ። እንደ ደረጃ ሽግግርም ይመለከቱታል (Palgi and Henry, 1984) ።

በየትኛውም ማህበረሰብ አንድ ሰው ሲሞት ቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ ጎረቤት ለደረሰው አደጋ የየራሳቸውን ምላሽ ይሰጣሉ። አፈፃፀሙ እንደ ባህሉና እንደ አካባቢው ሊለያይ ይችላል። በሞት ጊዜ የሚከወኑ ሥነሥርዓቶች እንደማንኛውም የባህል ዘርፍ ከትውልድ ትውልድ፣ ከቤተሰብ ለልጅ ሲተላለፉ የቆዩ ናቸው (Jeff, 2008:353) ፡፡

ሞት በርካታ የማህበራዊ፣ የእምነትና የባህል ፍልስፍና ሀሳቦች ምንጭ ሆኖም ይታያል። ከሞት በኋላ ስላለው ህይወት፣ የዳግም ልደት፣ የገነትና የገሃነም፣ የመፍረስና የመዳን፣ የሚችና በህይወት ያሉት ቤተሰቦችና ወገኖች ግንኙነት እና ሌሎችም ሀሳቦች በሞት ጊዜ እየተነሱ ይገመገማሉ (Kaufman, 2005:223) ፡፡

ከላይ እንደቀረበው ሞት ለሁሉ ፍጡር የጋራ ክስተት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሕዝቦች ሞትን እንደ ባህላቸው በተለያየ መንገድ ይመለከቱታል፡፡ ይህ የተለያየ አመለካከትም የሞት የተለያዩ ገፅታዎች አመልካች ክዋኔዎች መኖራቸውን ያሳያል፡፡ Alambi የተባለ ኬንያዊ የመስኩ ተመራማሪ The Ambayyole Dirge : "Escorting" the Dead with Song and Dance በሚለው ጥናታው ጽሑፉ አብዛኛው የአፍሪካ ሕዝብ ሞት የሰው ልጅ የህይወት መጨረሻ ሳይሆን ወደ ሌላ ህይወት መሸጋገሪያ ነው ብሎ እንደሚያምን ገልፆ ጥናቱ ባተኮረበት ማህበረሰብ የለቅሶው ክዋኔና የቀብር ሥርዓቱ እንደሚቹ የኑሮ ደረጃ፣ የሀብታሙ የተከበረ፣ የደመቀ፣ የደሃው ደግሞ የተቀዛቀዘ ነው፤ ክዋኔው የለቅሶ ሳይሆን የኑሮ ማሳያ ነው (Alembi,www.folklore 2013) ብሏል፡፡

በሊበን መጫ አሮሞ ዘንድም፣ ሞት ቀኑን ጠብቆ የሚመጣ ክስተት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህም ሆኖ በጥናቱ አካባቢ በየለቅሶው ሥርዓት የሚነገረው ተረክ እንደሚያስረዳው ሞት ሦስት ዓይነት ነው ፡፡

> Dutii kun gosa sadii jedhu. Tokko bosbostuu, lamaffaan tortortuu, sadaffaan tottoltuudha jedhan jedhu. Bosbostuun kun dulloomani, "eeessaanan du'a arga" jedhanii du'a ittikadhatani. Tortortuun ammoo otoo hinfuudhiin, otoo hinuumiin, otoo toora hindarbiin yoo du'ani. Tottoltuun ilma fuusissee, akaakayyuu argee, intala heerumsiisee, ilma daarii brsiisee, lammi, wagana barsiisee nama du'e, otoo waggaa lama sadii jiratee kan jedhaamu duutisaa tottoltuudha.[2]

የተረኩ ፍች እንደሚያስረዳው፣ ሞት ሦስት ዓይነት ነው፡፡ "bosbostuu" (ፍርክርክ፣ ድቅቅ ከማለት፣ በእርጅና የሚመጣ ) ይህ ዓይነቱ ሞት አርጅተው "ሞትን በየት ባገኘሁ" ብለው በሚለምኑበት ጊዜ የሚከሰት ዓይነት ነው "Tortortuun" (መጥፎ ሞት) ይህኛው ደግሞ ሳያገቡ፣ ሳይወልዱ፣ ዘር ሳይተኩ ተቀጥፎ ማለፍ፤ "Tottoltuun" (ጥሩ ሞት) ወንድ፣ ሴት ልጅ ድሮ፣ አያት አይቶ፣ ለልጁ ዳር ድንበሩንና ወገኑን አሳውቆ የሞተ እና ለአፍ "ምናለ ሁለት ሦስት ዓመት እንኳ በኖረ ኖሮ" የሚበልለት (ሞቱ እምብዛም የማይቆጭ) ነው። ይህን ተረክ በመንተራስ ነው ጥናቱ የተከናወነበት አካባቢ ሕዝብ ሞትን በሦስት ከፍሎ ይገልፃል ለማለት የደፈርኩት። በምልከታ እንደታየው በተላያዩ እድሜ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሲሞቱ በማስተዛዘኛ ወቅት በጫወታ ጫወታ መሀከል በተረኩ ውስጥ የተነሱ ሃሳቦች ተደጋግመው ይነሳሉ። ይኸውም ቤተሰብ ሀዘን ሲያበዛ፣ በሞቱ ሰበብ እርር ድብን ብለው ሲናገሩና ሲያለቅሱ አስተዛዛኞች፣ የሟች እድሜ ገፋ ያለ ከሆነ፣ ወንድ ሴቱን ድረው አያት ቅድመ አያት ያዩና ጥሩ ኑሮ የኖሩ ከሆኑ ለሀዘንተኛው "Gahe! Dhiisaa maalii? Maaltu itti hafe? Waan hundumaa arganiiru gadda qabbanessaa"- "በቃ! ምንድነው? ምንቀራቸው? ሁሉንም አይተዋል፤ ሀዘኑን በልክ አድርጉ"

---

[2] አቶ በዳዳ ሆርሴ ቃለመጠይቅ ሰኔ 16 ቀን 2006 ወሊሶ ወረዳ)

ብለው ሀዘንተኛ ሲመክሩ ይሰማል። የሞቱት፣ ያረጁ፣ የጃጁ፣ በህመም ማቀው፣ ለአስታማሚ የሰለቹ ከሆኑ ደግሞ፣ "ሞቱ አይባልም፣ መለቀሱም እኮ ዘፍኖ ስለማይቀበር ነው፣ ተገላገሉ" ይላሉ በሟቹ አሟሟት ላይ አስተያየት የሚሰጡ፡፡ ወጣት፣ ያልተደረ/ያልተዳረች ወልዶ/ዳ ዘር ያልተካ ከሞተ/ች፣ "ተቀጨ/ተቀጨች፣ የሚያሳርር ሀዘን ደረሰ፣ ከአንጀት የማይወጣ ሀዘን ገጠመ" ተብሎ ይነገራል።

አንድ ሰው በምን ሞተ? ሲባል "ታሞ፣ በድንገት፣ በሰው እጅ፣ በሌሎች አደጋዎች" ተብሎ ይገለፃል፡፡ በይፋ በሚደረጉ ቃለመጠይቆች የሞት ሰበቦች እድሜ/እርጅና፣ ህመምና አደጋዎች እንደሆኑ የተገለፁ ሲሆን፣ ሕዝብ መሃል ሲገባ በሚደረገው ውይይትና የማስተዛዘን ሂደት ወቅት በሚንሻራሸሩ ሃሳቦች የሚጠቀሱ የሞት ምክንያቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ መልከመልካም/ቆንጆ ወጣት ድንገት ቢሞት/ብትሞት "Ija namattu ajjeese, akka namaatti hin uumamnewoo!"- "የሰው ዓይን ነው የገደለው /የገደላት። እንደሰው አልተፈጠረም/አልተፈጠረችም፡፡" እንዲሁም በሙሽርነት ዘመን የሞት አደጋ የደረሰባቸውም በሰው ዓይን ነው የሚሉም አሉ፡፡ ህፃናት ሲሞቱም እንዲሁ የሰው ዓይን ነው ተብሎ የሚነገርበት ሁኔታ ይታያል፡፡ ከዚህ ሌላ የሞት ምክንያት የሚባለው ከሰው የተጣላ ሰው በአጋጣሚ ሲሞት፣ Itti booyani imimmaan namaa akkana nama godh"አልቅሰውበት፣ የሰው እምባ እንዲህ ነው የሚያደርገው፤ ተረግሞ ነው" የሚባልበት አጋጣሚ አለ፡፡ እነዚህ የሰው ዓይንና እርግማን የሚባሉ ምክንያቶች በይፋ የሚነገሩ ሳይሆን እርስበርስ ስለተከሰተው ሞት ምክንያት ሲጫወቱ በድብቅ የሚሉት ነው፡፡ እነዚህ አመለካከቶች ለሞት መንስኤ የሆኑ ችግሮችን መርምሮ ከመረዳት አንፃር ያለውን ግንዛቤና እውቀት የሚያንፀባርቁ ናቸው።

በምንም ምክንያት ይሁን ሞት ሲመጣ ልጅ፣ አዋቂ፣ ሴት፣ ወንድ ብሎ ባይለይም በሊበን መጫ ኦሮሞ ባህል ሞት ሲከሰት አለቃቀሱና የሀዘን ሥርዓቱ እንደ ሟች እድሜና ደረጃ ይለያል፡፡

> Jaarsi guddaan yoo du'e fakkaataan hiriyaansaa gaachana qabatee bahee, farda fe'atee fokkoree/dhaadatee, oofan jedhee gaggeessa. Dubartiin gudoon, gaariin yooduutes akkasuma. Drgageessi yoo du'e umriinsaa giddugaleessa yoo ta'e fardi hinfe'amaaf, dhaadachuu hiriyaasaatu dhadtaaf malee jaarsi hindhaadatuuf. Ijolleen xixinnoon yoo duute ammoo dhaadachuun, oofanii dhiituun hinjiru boo'aniituma gaggeessu jechaadha[3]፡- ትልቅ አዛውንት ከሞተ የእድሜ አቻዎቹ ፈረስ ጭነው፣ ጋሻ ይዘው፣ ፎከረውለት፣ ኦፈን ብለው አስለቅሰውለት፣ ይሸኙታል፡፡ አዋቂና ጥሩ ሰው የተባለች ሴት ስትሞትም እንዲሁ ነው። በእድሜው መሃከለኛና ልጅ እግር ከሞተ ፈረስ ይጫንለታል፤ የእድሜ አቻዎቹ ይፎከሩለታል፤ አዛውንት ግን ለልጅ እግር ሰው አይፍከርም፣ ኦፈንም

[3] አቶ ተሾመ ዘውዴ ቃለመጠይቅ ሰኔ26 ቀን 2006 ወንጪ ወረዳ ፡፡

አይባልለትም፡፡ ትንንሽ ልጆች ቢሞቱ ደግሞ አይፎከርላቸውም፣ ኦፈንም አይባልላቸውም እንዲሁ ተለቅሶ የቀብር ሥርዓት ይፈፀማል ማለት ነው።

በለቅሶ ግጥም ላይ ጥናት ያደረገው ኬንያዊው አለምቢ ከላይ በተጠቀሰው ፅሑፉ እንደሚለው ዓይነት በሊበን መጫ ኦሮሞ፣ በደሃና በሀብታም ለቅሶ ክዋኔ መሃከል ልዩነት የጎላ አይደለም። ለለቅሶው ታዳሚዎች የሚደረገው መስተንግዶ ግን ሊለያይ ይችላል፡፡ የአለቃቀስ ክዋኔውን ምጣኔ ሀብቱ ሳይሆን የሟቹ የማንነት ጉዳይ ይወስነዋል፡፡ በተለያዩ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔዎች ላይ በተደረጉ ምልከታዎች ሟች የወጣበት/የወጣችበት ማህበረሰብ ማንነት፣ ሟች በህይወት ዘመኑ/ኗ ለቤተሰብ፣ ለወገን፣ ለጎረቤት ያለው/ያላት አመለካከትና አቀራረብ የአለቃቀስ ክዋኔውን ሊያደምቀው ወይም ሊያቀዘቅዘው እንደሚችል መለየትና መገንዘብ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ በወንጪ ወረዳ በዳሪያን አካባቢ አቶ በዳዳ እጀታ የተባሉ ሰው ትዳር የላቸውም ልጆች የላቸውም፣ ከወንድሞቻቸው ተጠግተው የሚኖሩ ሆነው ሳለ፣ ሲሞቱ ግን የለቅሶዋቸው ሥርዓት ሀብታም፣ ባለትዳርና የልጆች አባት ናቸው ከሚባሉት ሰዎች ለቅሶ ባልተናነሰ ሁኔታ ደምቆ፣ በርካታ ሰዎች ተሳትፈውበት ታይቷል፡፡ ይህ የሟቹን ሀብት ሳይሆን ውሎና ተግባሩን ያሳያል፡፡ ለቅሶዋቸው ላይ ፉከራም ኦፈንም ተከውነው በደመቀ መልክ ቀብራቸው ተፈፅሟል፡፡ ሲለቀስላቸውም ውሎአቸውና ተግባራቸው እየተጠቀሰ ነበር፡፡ በሌሎች ለቅሶዎችም የሚፎከረውና የሚለቀሰው የሟች የውሎ ሁኔታ ትኩረት ተደርጎበት ስለሆነ በሊበን መጫ ኦሮሞ ውሎ ወሳኝነት አለው ማለት ይቻላል፡፡

## ቅድመ ቀብር ሥርዓት

ጥናቱ በተካሄደባቸው ወረዳዎች አንድ ሰው ታሞ አልጋ ላይ ከዋለ፣ ልጆች ካሉት፣ ወይም ወገን የሆነና አብሮ የሚኖር ሰው ካለ ችግሩን ተመልክቶ ይንከባከበዋል[4]፡፡ በህመሙ መክንያት የቆሸሸ ልብሱን ያጥቡለታል፣ መኝታውን ለታማሚ በሚሆን መልኩ ያስተካክሉለታል፤ ለህመምተኛ የሚሆን ምግብ ያቀርቡለታል፡፡ በእንዲህ ሁኔታ ሲታገዝ ውሎ ሲያድር ጎረቤቱና ቤተዘመዱ መጀመሪያ እንደ ባህሉ "Waaq siyaamaaru" – "እግዚአብሄር ይማርህ" ብለው ይጠይቃሉ፤ ቡና ተፈልቶ ታላቅ የሆነ ሰው "daraaraa/biqila[5] fidaa waaq kadhannaafii" ተብሎ ከቀረበ በኋላ ይፀለይለታል፡፡ ሳይሻለው ቀርቶ ህመሙ ከቀጠለ ይበጃል የተባለ ባህላዊ ወይም ዘመናዊ ህክምና ወስደው እንዲረዳ ያደርጋሉ ፡፡

የህመሙ ሁኔታ ተስፋ አስቆራጭና ለሞት የሚያበቃ መስሎ ከታየ አንዳንድ ዝግጅቶች ይደረጋሉ ፡፡ በተለይ ታማሚው ትልቅ ሰው ከሆኑ አጥር ማጠናካከር፣ ቤትና ደጃፉን ማፅዳት በቤት ውስጥ የሚያስፈልጉ ከዕድሮች ሥራ ውጭ የሆኑት ጉዳዮች ላይ ተነጋግረው ዝግጅት ያደርጋሉ (ለእንግዳ መሸኛ እርድ ካስፈለገ)። በዚህ ወቅት ከጎረቤት የቅርብ የሆናና ሞት ቢከሰት

---

[4] በምልከታና በቃለመጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች

[5] ደራራ/ቢቂላ ማለት መመረቂያ ለምለም ነገር ማለት ነው ለዚህ ተግባር የሚወከሉት ማር ወይም በቤት የተጠመቀ ጠላ ወይም አረቄ ወይም ሰርዶ ሳር ነው፡፡ እነዚህ ቁሳቁሶች በባህሉ መመረከቂያ መፀለያ ናቸው፡፡

አስክሬን የማስተካከል እውቀት ያለው ሰው ብዙውን ጊዜ አብሮ ይሆናል ወይም ርቆ አይሄድም ። ለወንድ ታማሚ ወንድ ለሴት ደግሞ ሴት ለማስተካከል እንዲቀመጡ ወይም ችግሩ ሲከሰት እንዲጠሩ ይደረጋል፡፡

እንዲሁ እየተረዳና ዝግጅት እየተደረገ ቀኑ ደርሶ እስትንፋሱ እንደተቋረጠች የሰማው ጎረቤት ሁሉ ይሰበሰባል፤ "hollaan ni birmata"፣ አስክሬኑ ተገንዞ፣ ታጥቦ፣ ከሳጥን ተከቶ ቦታ ከያዘ በኋላ ይለቀሳል፡፡ በባህሉ በተገኘ ሰዓት ሁሉ አይለቀስም፡፡ ቤተሰብና የቅርብ ዘመዶች ግን ድምጽን ዝቅ አድርገው እያለቀሱ እርም ያወጣሉ፡፡ ጠዋት ለሞተና ቀብሩ በማግስቱ ለሆነ ሰው አስከሬኑ እንደተስተካከለ ይለቀሳል፤ ዘመድ አዝማድ እንዲ ደርስ ቀብሩ ውሎ ይደር ከተባለ ደግሞ ሲዘጋጁ ውለው በነጋተው ሊያስለቅሱ ይችላሉ፡፡

## የመርዶ መልዕክት ለዘመድ አዝማድ መላክ

አስክሬኑ ከተስተካከለ በኋላ ቤተሰብ ተወያይቶ የቀብሩ ቀን ይወሰናል፡፡ በማስከተል ወደየዘመድ አዝማድ እርማቸውን እንዲያወጡ መርዶውን የሚገልፅ ደብዳቤ6 ወይም የቃል መልዕክት በመልእክተኛ እንዲላክ ይደረጋል፤ በመልዕክቱ ላይ የሚቹ ስም፤ ቀብሩ የሚፈጸምበት ቀንና ሰዓት፤ የቀብሩ ሥፍራ፤ መልዕክቱን ያስተላለፈ ሰው ስም በትክክል ይገለጻል፡፡

ይህን ተግባርና ሌሎች የመስተንግዶ ጉዳዮችን ለማስፈፀም ሕዝቡ በየአካባቢው ዕድሮች አቋቁሟል፡፡ ዕድሮችን የሚያቋቁሙት በሞትና ሀዘን ጊዜ ለመተጋገዝና ለመረዳዳት ነው ፡፡ በሊበን መጫ ኦሮሞ ሁለት ዓይነት ዕድሮች አሉ ፡ እነርሱም (Moodii) ሞዲና (Golobee) ጎሎቤ ናቸው፡፡ ሞዲ የዕድሩ ባልደረባ ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ የተለያየ እንቅስቀሴ የሚያደርግና በቀብር ዕለት ሰፊ ሥራ የሚሠራ ሲሆን፣ ጎሎቤ በአቅራቢያ የሚገኙ ጎረቤታሞች ተደራጅተው የሚያቋቁሙት ከሀዘን እስኪነሱ የማስተዛዘንና የመስተንግዶ አገልግሎት የሚሰጥ የዕድር ዓይነት ነው[7]።

ከየወረዳዎቹ በቃለመጠይቅና በምልከታ በተሰበሰቡት መረጃዎች መሠረት ሰው ሲሞት የሟችን ዜና እረፍት ለወገኖቹ የሚያደርሰው ዕድር (ሞዲ) ነው፡፡ ዘመዶቹ ይኖራሉ ወደ ተባለ አቅጣጫ ሁሉ፣ ከቤተሰቡ ስለሞቱ የሚገልፅ ደብዳቤ ይድረስልን ላሉት ሁሉ ይላካል። የተጠሩት ሁሉ በቀብሩ ላይ እንዲገኙ በሚል ከሁለት አስከ ሦስት ቀን አስከሬን በቤት እንዲቆይ ይደረጋል፡፡ ከዚህም ሌላ በእድሩ እያንዳንዱ አባል በሚጥለው መዋጮ ለቀባሪ ማስተናገጃ እህል ተገዝቶ ይቀመጣል፡፡ የሬሳ ሣጥንና የከፈን ጨርቅም እንዲሁ ተገዝቶና ተዘጋጅቶ ይቀመጣል፡፡ የሬሣ ሣጥንና የከፈን ጨርቁ ከዕድር ንብረት ያዥ ወጥቶ አስከሬን ታጥቦ፣ ተከፍኖ፣ በሣጥኑ ተከቶ ይዘጋጃጃል፡፡ እህልም ወጥቶ ይፈጫል፤ ለእንግዳ (ለቀባሪ) ማስተናገጃ በሚሆን መልኩ በስሎ

[6] አቶ ዳበሳ አባመልካ ከወንጪ ወረዳ ቃለመጠየቅ ባደረኩላቸው ወቅት እንደተናገሩት መጻፍ የሚችል ተፈልጎ በተገለጸው መልዕክቱ ተጽፎ መልእክተኛው ይዞ ይሄዳል፡፡ ደብዳቤ መላክ ክብር አመልካች፣ በቃል ነገሩኝ ማለት ነገሩን ስለሚያቀለው ክብደት ለመስጠትም ነው ብለዋል፡፡

[7] የወሊሶ ፣ የወንጪ እና የዳዎ ወረዳ መረጃ አቀባዮች ከሰጡት መረጃ

ይዘጋጃል። እያንዳንዱ የሞዲ አባል ለለቅሶ ቤቱ ምግብ ዝግጅትና የቡና ማፈያ አገልግሎት የሚውል ማገዶ (Qoraan Moodii) አንዳንድ እስር እና የቡና ቁርስ ቆሎ አንዳንድ ኪሎ ግራም የሚገመት(አንድ ጆግ)፤ ሁለት ሁለት በርጩማ ወይም አንድ አግዳሚ ከየቤታቸው ይዘው ይቀርባሉ፡፡ የቀብሩ ዕለት ድንኳን ይጣላል፤ ተጨማሪ በርጩማዎች፣ የተለያዩ ወንበሮች ተሰበስበው ይደረደራሉ፡፡ በአካባቢው ለማሰለቀሻ የሚገለገሉበት ሜዳማ ሰፊ ቦታ ላይ ለአስከሬኑ ማሳረፊያ መጠነኛ ዳስ ይጣላል ፡፡

## ጉድጓድ ቁፋሮ (Laffa tuqaa)

የቀብር ዕለት "yeroo bobbaa horii" ሦስት ሰዓት አካባቢ ከብት በሚሠማራበት አካባቢ እንደማለት ነው፤ ለጉድጓድ ቁፋሮ ተረኛ የሆነ ቡድን ከሞዲ አባላት ይላካሉ፡፡ ከተላኩት ሰዎች ጋር የሟች ልጅ ወይም አባት ወይም ወንድም እርሱም ከሌለ የቅርብ ሰው መጀመሪያ በተመረጠው የቀብሩ ቦታ ጉድጓዱን ቆፈር አድርጎ ማስጀመር አለበት። አለበለዚያ አይነኩትም ፡፡ ይህ ቆፈር አድርጎ የማስጀመሩ ሥርዓት "Lafa tuqaa" ይባለል፡፡ አባት ከሞተ ታላቅ ልጅ ወይም ወንድም ኃለፊነት ወስዶ ያስጀምራል፡፡ ማንም እንዲሁ ተነስቶ የማንንም ጉድጓድ እራሱ ጀምሮ አይቆፍርም "Ooda" –ባህላዊ ክልከላ አለው። የሞትን መጥፎ መንፈስ ወደ እራስ መጥራት ነው ተብሎ ስለሚታመን፤ ይከለከላል ፡፡ ድርጊቱ ለሚወከለው የቤተሰቡ አባል ግን ኃለፊነት መውሰድ ነው፡፡

## ማስለቀስ (Boochisuu)

በቃለመጠይቅ ከተሰበሰቡት መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው በቀብሩ ዕለት ወደ አራት ሰዓት አካባቢ በማስለቀሻው አካባቢ ላይ ወንበር በብዛት ወጥቶ ጥግጥ ላይ ይደረደራል፡፡ አስከሬኑም ወጥቶ በተዘጋጀው ዳስ ውስጥ ያርፋል፡፡ በዙሪያው ቤተሰብ ከቦ የሚቀመጥበትና የሚያለቅስበት አግዳሚ ወንበሮች ይደረደራሉ። በዳሱ በር ላይ ሟች በህይወት እያለ/እያለች ይለብሳቸው/ትለብሳቸው የነበሩ የክት አልባሳት፣ የወግ ቁሳቁሶች እንደ ጦር፣ ጋሻ፣ ለምድ፣ ጭራ የክብር በትር ይሰቀላል፡፡ ፎቶ ካላቸው በዳሱ ውስጥ ይሰቀላል፤ በእጅም ተይዞ ይለቀስበታል፡፡ አንዳንድ በምልከታ በተቃኙ የለቅሶ ክዋኔዎች ላይ ከነዚህ ቁሳቁሶች በተጨማሪ ጣርሙስ ባህላዊ አረቄና ባለክዳን ሳህን ምግብ ተደርጎበት ተሸፍኖ ከዳሱ ጎን በውጭ በኩል ይቀመጣል፡፡ እነዚህ በዳሱ አካባቢ የሚቀመጡ ቁሳቁሶች ከአልባሳት ጀምሮ ያሉት የራሳቸው ትርጉም አላቸው፡፡ አልባሳቱና የሚይዙዋቸው ቁሳቁሶች የለቅሶው እድምተኞች ሟችን በአልባሱ ደምቀው አደባባይ የዋሉባቸውን አውዶች እያስታወሱ እንዲያስቡዋቸው፣ እንዲያለቅሱ ለማድረግ ሲሆን፣ አረቄና ምግብ የያዘው ሳህን ሟች እንግዳ ተቀባይና አስተናጋጅ እንደነበሩ ለማሳየት ነው።[8] ዳስ በተጣለበት ቦታ ከላይ የተገለፁት ክዋኔዎች ከተከወኑ በኋላ በዳሱ ፊትለፊት ማስለቀስ ይጀመራል፡፡ አለቃቀሱም ዓይነት አለው፡፡

[8] አቶ ዳበሳ አባመልካ በቃለመጠይቅ ከሰጡት መረጃ የተወሰደ

## በዝግታ ማልቀስ (Asaasii baasuu)

ለቅሶውን ሰምቶ ከየአቅጣጫው የሚመጣው ዘመድ፣ ወገንና ወዳጅ በህብረት ይንቀሳቀሳል፡ የሞት መርዶ የተላከበት፣ ቤተሰብ፣ ቤተዘመድ እና ወገን ለብቻው አይመጣም ጎረቤቱን ወይም እድሩን ያስከትላል፡፡ ከሟች ጋር ዝምድናና ዕውቅና ሳይኖራቸው የጎረቤቶቻቸው ወይም የጓደኞቻቸው አጃቢ ሆነው የመጡ ከማስለቀሻው ሥፍራ ሲደርሱ ሁሉም በህብረትና ዝግ ባለ ድምፅ፣ በአብዛኛው አፋቸውን ሸፈን አድርገው ድምፁ በህብረት ሆኖ ስለሚደራረብ አምብዛም አይደመጥም፡፡ ከሚደመጡት "Ani bade! Tasa baddee...Anaani anaani haadhoo koo..., Obbolee koo...haadha koo...Abbaa koo ..."ትርጉሙ፡ እኔ ልጥፋ፣ ድንገት ጠፋህ፣ እኔን! እኔን! የእናቴ ልጅ ... እናቴ.. አባቴ... የመሳሰሉትን እያሉ የሟቹን ማንነት እየጠቀሱ በቀስታ እርምጃ ከዳሱ ፊት ለፊት ሁለቴ ሦስቴ ተመላልሰው ያለቅሳሉ። ይህ ዓይነቱ አለቃቀስ "Asaasii baasuu" ይባላል፡፡እርም ማውጣት እንደማለት ነው። ወደለቅሶ ቦታ ሄዶ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚገለፅ የኀዘን ስሜት ነው። ሟችን አወቁም አላወቁ፣ እንባ ወጣቸውም አልወጣቸው፣ እንዲህ በህብረት ድምፅ አሰምቶና ተመላልሶ/ ወደ ግራና ቀኝ ተዟዙሮ ማልቀስ በባህሉ የግድ ነው፤ አለበለዚያ ቂም አላቸው ተብሎ ይታሰባል ፡፡

በመቀጠል በህብረት መጥቶ ካለቀሰው ውስጥ የተለያዩ የአለቃቀስ ስልት በመከተል የተሰማውን የሀዘን ስሜት የሚገልፅም አለ፡፡ አንዳንዱ ሬሳ ሣጥኑ ላይ ተኝቶ፣ ዳብሶ የሟችን ስምና ውለታ እየጠቀሰ እያለቀሰ ሀዘኑን ይገልፃል፤ ሟች፣ ለተቸገረ ደጀን፣ ለጋስ፣ ጠያቂ፣ ለችግር ጊዜ ፈጥኖ ደራሽ፣ አበዳሪ፣ መካሪ፣ አስታራቂ፣ ዘመድ ወዳድ፣ ዘመድ ሰብሳቢ እንደነበር እየገለፁ ከዚህ በኋላ ይህ ሁሉ አስተዋፅዖው እንደሚቀርና እንደሚጓደልባቸው እየተንሰቀሰቁ የሚገልፁም አሉ፡፡ ይህን ተንሰቅስቆ የማልቀስ ክዋኔን "hiqqisani bohuu" ይሉታል ፡፡

## በዜማ እየዘለሉ ማስለቀስ (Oofan)

ሌላው በህብረት የሚለቀስበት የአለቃቀስ ስልት "oofan" የሚባለው የአለቃቀስ ዓይነት ነው። ይህ የለቅሶ ዓይነት በአብዛኛው ለአዛውንቶች፣ ለጀግኖች፣ ለታዋቂ ሰው የሚለቀስ ነው ተብሎ ይነገራል፡፡ በግል ከማስለቀስ ቀጥሎ የሟች ጓደኛና የቅርብ ሰው የሆኑ ተመራርጠው የሚያለቅሱበት ነው፡፡ በዚህ ዓይነቱ የለቅሶ አከዋወን የሚያስለቅሱትም በዕድሜ ጠና ያሉ የሟች ጓደኞችና የዕድሜ አቻዎች ናቸው፡፡ ኦፈን ዜማና ምት አለው ፡፡ በአውራጅና ተቀባይ ዓይነት እየተቀባበሉ በትሮቻቸውን ወደላይ ይዘው በረድፍ በረድፍ ሆነው በእግር እየረገጡ በዜማ ያለቅሳሉ፡፡ በዚህ የለቅሶ ክዋኔ ሴቶች በተቀባይነት በዜማው ምት እየረገጡ ይሳተፋሉ፡፡ ይህ የአለቃቀስ ስልት በሽመግሌዎች እንደተከለከለ የሚገልፁ መረጃች አሉ። ምክንያቱም "hundumtu ka'ee eenyumaafuu fiigee seera waan balleessee sirba waan fakkeesseef isaafi qalanii keessummaa gaggeessuun kunis ummata dorgommi keessa waangalcheef duutis waan ammaateef dhoowwineerra .

Ammas darbee darbee hinmuldhata"[9] ፡- "ሁሉም ተነስቶ፣ ለማንም፣ የአለቃቀስ ሥርዓቱን ቀይሮ እየሮጠ ዘፈን ሲያስመስለው፣ ከብት አርዶ እንግዳ መሸኘቱም በሰው መካከል ፉክክር ስለፈጠረ፣ እንዲህም ሲደረግ ለቅሶው ስለበዛ ሽማግሌዎች ተነጋግረን ኦፈንና ከብት አርዶ ለቀባሪ ማብላት ይቅር ብለናል" ብለዋል ፡፡ ይሁን እንጂ በምልከታ ማረጋገጥ እንደተቻለው የአለቃቀስ ስልቱ እየተከወነ ይገኛል፤ አርዶ ለቀባሪ ማብላቱም አቅሙ የፈቀደለት አልተወዉም፡፡

| አውራጅ | ተቀባይ | ትርጉም |
|---|---|---|
| Oo…fan oo…fan | oo…fan | ኦፈን…ኦፈን |
| Oo…fan oo…fan | oo…fan | ኦፈን…ኦፈን |
| Abbaan biyyaa du'ee eenyutu walgaafata | oo…fan | የሀገሩ አባት ሞተ<br>ማን ይጠያየቃል |
| Abbaan biyyaa du'ee eenyutu walgaafata | Oo…fan | የሀገሩ አባት ሞተ<br>ማን ይጠያየቃል |
| Oo…fan oo…fan | Oo…fan | ኦፈን…ኦፈን |
| Oo…fan oo…fan | Oo…fan | ኦፈን…ኦፈን |
| Bayeessa koo | Oo…fan | የኔ ጥሩ ሰው |
| Jaarsa biyyaa | Oo…fan | የሀገር ሽማግሌ |
| Abbaa maatii | Oo…fan | የቤተሰብ ኃለፊ |
| Abbaa biyyaa | Oo…fan | የሀገር ሽማግሌ |
| Oofaa soolee | Oo…fan | የሶሌ ጦር[10] |
| Abbaan mirgaa | Oo…fan | ጀግናው |
| Lolaati oolee | Oo…fan | ሲዋጋ ዋለ |
| Abbaan duulaa du'ee eenyu waatwaachisa | Oo…fan | መሪ ሞተ ማን ያጨናንቃል/ ለጠላት ጋሬጣ ማን ይሆናል |

እነዚህ ከላይ የቀረቡ የኦፈን አለቃቀስ (ሙሾ አወራረድ) ስንኝኞች የሟችን ማንነትና ውሎ የሚያስረዱ ናቸው ፡፡ ሟች በአካባቢው ሕዝብ እንደመሪ የሚታዩ ጥሩ ሰው፣ የተጣላ አስታራቂ

[9] የወሊሶ መረጃ አቀባይ የሆኑ አቶ በዳዳ ሆርሴ
[10] ሶሌ-የእንጨት ዓይነት ነው

ሽማግሌ፣ የሀገር ዳርድንበር አስከባሪ፣ አዋጊ ጀግና እንደ ነበሩ የሚገልጹናቸው፡፡ ሌሎች የሟችን ማህበራዊ ህይወት የሚያሳዩ ስንኞችም አሉ ፡፡

**በፉከራ ማስለቀስ** (Himuu/Dhaadachuu)

"Himuu" ቀጥታ ትርጉሙ "መንገር" ሲሆን፣ በዚህ አውዱ ስለሟች ማንነት መተረክ፣ መንገር፣ ተግባሩን ጠቅሶ መፎከር ነው፡፡ ይኸውም ፡- የሟችን ደግነት፣ ጀግንነት፣ አርቆ አሳቢነት፣ ሰው ወዳድነት ታታሪነት፣ ሥራ ወዳድነት እየገለፁ፣ የዘር ግንዱን፣ ወገኑን እየጠቀሱ በፉከራ ወይም እየተረኩ፣ በእግር ወይም በፈረስ ላይ ሆነው በጋራ ወይም በተናጠል የሚያስለቅሱበት ስልት ነው፡፡ ብዙ ሆነው ፈረስ ጭነው የሚመጡት አልቃሾች በዚህ ዓይነቱ የአለቃቀስ ስልት ፈረሶቻቸውን እያዘለሉ ወዲያና ወዲህ (Danglaasaa) ጋልበው እየፎከሩ የተሰማቸውን የሀዘን ስሜት ይገልፃሉ፡፡ ለምሳሌ ጀግንነቱን በጆሮው ሎቲ፣ በጋሻው፣ በጦሩና በፈረሱ ሁኔታና በሌሎች በከወናቸው ተግባራት የሚገልፁት እንደሚከተለው እያሉ ነው፡፡

| | |
|---|---|
| Abalu harka kooti[11] | እገሌ እጄ አይደለም! |
| Kan gurri looti | ጀግና ጆሮው ሎቲ |
| Abbaa mootii | የጀግና ጅግና |
| Eessaan dhaqxu?! | የት ትወስዱት |
| Harki gachana | እጁ ጋሻ |
| Eeboon banbana | ጦሩ የሰላ |
| Bullon akkana | ቡሎ ፈረሱም እንዲሁ |
| Eessaan dhaqxu?! | የት ትወስዱት?! |
| Abbaa malaa | አባ መላው |
| Malaan gala | በመላ ያሸንፋል |
| Maa awwaallaa? | ለምን እንቀብራለን?! |
| Eessaan dhaqxu? | የት ትወስዱት ?! |
| Dutaa akka leencaa | እንደ አንበሳ የሚያገሳ |
| Butaa akka Amaaqexaa | እንደ ነብር የሚመነትፍ |
| Dallanaa akka Qeerrensaa | አኩራፊ እንደ አነር |
| Isa diina jilbeeffachiisu | ጠላት አንበርካኪው |

[11] ይህ ስንኝ ሌላም ተርጓሜ ሊኖረው ይችላል፡፡ ሟች ኮት ለባሽ፣ ዘናጭ ነበር ለማለት፡፡

| | |
|---|---|
| Isa diira ofirratti finceessisu | ጀግና ባዩን የሚያሸና |
| Abbaa minishirii | ባለምንሽሩ |
| Qabataa albeenii | አልቤን ተሸካሚው |
| Gooftaa Mosolonii | የሞሶሉኒ ጌታ |

በዚህ ከላይ በቀረበው የ”ሂሙ” ወይም የሚች ያለፈ ጀብዱ/የጀግንነት ሥራ ትረካ ውስጥ የተገለፀው ሥራ በርካታ ነው፡፡ ጀግንነቱ የተገለፀው በሎቲው፣ በጋሻውና በፈረሱ ዓይነት ነው። በባህሉ ሁሉም ወንድ ሎቲ አያደርግም፡፡ ጥናቱ በተካሄደበት ሊበን መጫ አርሞ አንድ ወንድ ሎቲ የሚያደርገው በገዳ ሥርዓት በየስምንት ዓመቱ የሚደረገውን የስልጣን ቅብብሎሽ ጠብቆ አባቱ ባከበረው አርባኛ ዓመት በተራው ሥርዓቱን ተቀብሎ በሚደረግ የደረጃ ሽግግር ሥርዓት ከፍፃሜ አድርሶ ነው፡፡ ስለዚህ የዚህን ደረጃ ምልክት የሆነውን ሎቲ ያደረገ ሰው ሲሞት ደረጃው ላይ መድረሱ በምልክቱ ተገልፆ ይነገርለታል፤ ይለቀስለታል፡፡ እንዲሁም ጀግንነቱ ይይዛቸው በነበሩ መሳሪያዎች፣ በኃይለኛ እንስሳት ባህሪ እየተነገረለት ይፎከራል፡፡

የሚከተሉት የፉከራው ስንኞች ስለሚቹ በቤቱ ሆነ በደጁ ጥሩ ሰው መሆኑ፣ ቢናገር የሚያምርለት ማለትም ተናግሮ ማሳመን የሚችል፣ የሚያስታርቅ፣ ቢያርስ ምርት የሚሆንለት፣ ቢነግድ የሚሳከለት መሆኑ፣ ሴቷን ልጁን ወንዱንም የዳረ፣ የተከበረ፣ የሚወደድ የጥሩ ሰው ምሳሌ መሆኑ የተገለፁበት ናቸው ፡፡

| | |
|---|---|
| Bayeessa mana tole, | ጥሩው ሰው በቤቱ ደግ |
| Bayeessa ala tole | ጥሩው ሰው በደጅም ደግ |
| Namicha dubbannaan dubeen tole | ቢናገር የሚምርለት |
| Namicha qonnaan biqilli tole | ቢያርስ ምርት የሚሆንለት |
| Namicha nagdnaan nigdiin tole | ቢነግድ ንግድ የሚሆንለት |
| Namicha namooma qabu | ጥሩ ሰብዕና ያለው |
| Qotataa Koo! | የኔ አራሽ |
| Qotatee manasaa quubsate | ቢያርስ ቤቱን አጥግቦ |
| Qotee bela fageesse | አርሶ ረሃብ አጠፋ |
| Dongorraan jabeesseeti | ቢተክል አጠንክሮ |
| Dubbannaan barecheeti | ቢናገር አሳምሮ |
| Darbanaan fageesseeti | ቢወረውር አርቆ |
| Kan fuudhu fuusifate | የሚያገባውን ድሮ |

| | |
|---|---|
| Kan heerumtu heerumsiifate | የምታገባዋን ድሮ |

ቀጥሎ ያሉት የሂሙ/ፉከራ ስነኞች በወንጪ ወረዳ ሀሮ በሰቃ በተባለ ገጠር ቀበሌ የአቶ ጉርሜሳ ቀብር ላይ ከጓደኞቸው የተፎከረላቸው ሲሆን፣ በይዘት ከላይ እንደ ቀረበው የሚችን ማንነትና ውሎ የሚገልፁ ናቸው ፡፡

| | |
|---|---|
| Gurmeessaa koo | ጉርሜሳዬ |
| Gurraacha warra Waldoo | ጥቁሩ የነወልዶ |
| Gurracha garaa qulqulluu<br>Gurracha amma gurraa gahu | ጥቁር ሆዱ የጠራ<br>ጥቁር የሚወራለትን የሚያክል |
| Tulluu tulluu gubaa Xulee | የጡሌው ታላቁ ሰው |
| Qoricha gaafa rakkoo | የችግር ቀን መድሃኒት |
| Roorrisaa roorrisee bulu | እምብኝ ባይ ባመነበት ሚች |
| Ennaa daariin bade itti waaman | ዳር ድንበር ሲደፈር የሚጠሩት |
| Dhirsa Xaaliyaanii | የጣሊያን መድሃኒት |
| Gooftaa gaafa xiiqii | የቁርጥ ቀን /የጭንቅ ቀን ደራሽ |

በነዚህ ስኝኞች ውስጥ ያሉት ቃላት ቀጥታ ከሚነበቡበት የጠለቀ ፍች ያለቸው ሆነው ይታያሉ። ለምሳሌ ጥቁሩ የወልዶ ልጅ የሚለው ፡- ጥቁር የሚችን የቆዳ ቀለም ለመናገር የገባ አይደለም ከንፅህና ጋር በተያያዘ የሚባል ቃል ነው፤ ተንኮል የማያውቅ ለማለት የሚጠቀሙበት ነው፡፡ በኦሮሞ ጥቁር ቀለም ጭለማ አመልካች አይደለም፡፡ በአምልኮ ጊዜ "Waaqa Gurracha garaa qulqullu" ተብሎ የሚፀለየውም ንፅህናውን ለመግለፅ ነው፡፡ የወልዶ ልጅ የሚለውም ሚች የወጡበት ጎሳ ለማሳየት የተነገረ ነው። ሌላው "Gurracha amma gurraa gahu" ቀጥታ ትርጉሙ "ጥቁር ጆሮ የሚያክል" ነው፡፡ በለቅሶው አውድ ፉከራ ግን የጆሮ ፍች "የሚነገርለት" የሚለውን ቃል ይወክላል። የስንኙ ትርጉም ጥቁር/ንፁህ የሚነገርለትን የሚየክል ማለት ይሆናል፡፡ ይኸውም "የሚች ተግባሩ የሚባለውን ያህል ነው፣ ቃላቱ እንዲሁ የተደረደሩ አይደሉም የሚችን ተግባር ይናገራሉ ይወክላሉ" ነው። የሚች ተግባር የተነገርለትን ሀሳብ ይወክላል ማለት ነው፡፡ ሌሎቹ ስንኞች ደግሞ የሚቹን ጀግንነት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በችግር ጊዜ ፈጥኖ የሚደረስ፣ ጥቃት መሸከም የማይችል፣ ባለጌ ፊቱ የማይቆም፣ የወራሪ ሴራ በማክሸፍ እንደ መድሃኒት የሚታይ፣ ድንበር ሲደፈር የሚጠሩት የሚሉት ይህንኑ የሚችን የጀግንነት ውሎ የሚያሳውቁ የማስለቀሻ ፉካራው ስንኞች ናቸው፡፡ ባጠቃላይ "ሂሙ" ሚች በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ቦታ ገልፀው የሚያስለቅሱበት የአለቃቀስ ክዋኔ ነው፡፡

የሞተችው ሴት ከሆነችም በማንነቷ እንደ ወንዱ ይነገርላታል/ይተረክላታል፡፡ ይህ የመተረኩ ጉዳይ ለሁሉም ሴቶች አይከወንም፡፡ ከአካባቢው ልቀው የሚጠሩበት ተግባር ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ቸር ሆነው የተቸገረ የሚረዱ፣ በእንግዳ ተቀባይነታቸው የተነገረላቸው፣ ታታሪ ሠራተኛ፣ ቆጣቢና ባለሙያ መሆን አለባቸው። ቀጥሎ ያለውና ለሴት የተፎከረው ይንኑ ይዘት ያንፀባርቃል[12] ፡፡

| | |
|---|---|
| Kan namoomnishii gaarii | በማንነቷ ጥሩ የተባለች |
| Abbaa warraashitiif gaarii | ለባሏ ጥሩ ፣ |
| Kan buttaa qalchisiifte | ገዳ ያከበረችለት |
| Haadha maabara gaarii, | ጥሩ ማህበር ያላት |
| Ollaashiitiifs gaariidha, | ለጎረቤቷ ጥሩ |
| Hin olkaawwatti, kaamettiidhaa | የምትቆጥብ ባለሙያ ናት |
| Hin qoraafatti, | የወተት ዕቃዎችን በውጉ የምትይዝ |
| Qorobeenshi mirreedha | ጮጮዎቿ በየዓይነቱ ናቸው |
| Haannanshii mirreedha, | ብዙ ከብት የምተልብ ሀበታም ናት |
| Dhadhaanshii mirreedha | ቅቤ በየዓይነቱ የምታቀርብ |
| Caccabsaa tolfatti, cuukkoo tolfatti | የጨጨብሳ፣የጩኮ ባለሙያ |

በዚህ ለሴት በሚነገረውም ፉከራ ውስጥ ሟቿ በህሕይወት ዘመኗ ለጎረቤቷ፣ ለዘመዶቿ ጥሩ እንደ ሆነች፣ ጥሩ ማህበራዊ ሕይወት ያሳለፈች መሆኗን፣ በተለያዩ የባህል ምግቦች ዝግጅት ባለሙያ መሆኗን፣ መቆጠብ የምታውቅ መሆኗ የሚገለፅበት ነው፡፡ በቀረበው የፉከራ ቃላት ውስጥ ስለቅቤና ወተት የቀረቡት ሰፋ ያለ ፍች አላቸው፡፡ ይኸውም፡- ቅቤና ወተት ሊበዛ የሚችለው ሴትየዋ ብዙ የሚታለቡ ላሞች ስላሉዋት ብቻ አይደለም፤ የታለበው ወተት በጥራት (ታጥኖ)በአግባቡ የሚያዝ፣ የማይባክን፣ ቅቤውም የሚበዛው እንዲሁ እርጎ ከመሃል ሳይጠጣ በጥንቃቄ የሚጠራቀም ከሆነ ነው ቅቤ የሚበዛው፤ ባጠቃለይ ሴትየዋ ለነገ የምትልና የምትቆጥብ ናት ማለት ነው ፡፡

ሌላው የአለቃቀስ ዓይነት ስለሟች በአእምሮ እያሰላሰሉ ወይም የሚያለቅሰውን ሰው በመመልከት ጉዳዩን ከራስ ጉዳይ ጋር በማያያዝ ድምፅ ሳያወጡ ማልቀስ አለ፡፡ ይህን አለቃቀስ “Ofirratti bohuu” ይሉታል፡፡ ስለሟቹ በውስጣቸው፣ ለራሳቸው እየገለፁ በእንባ የሚታጠቡበት ነው፡፡ ይህን አለቃቀስ የሚጠቀሙ ተዟዙሮ ማልቀስ የሚፈሩ እንደሆኑ መረጃ ሰጪዎቹ ተናግረዋል፡፡

[12]አቶ ጎኛ ሃለቆ ቃለመጠይቅ ሰኔ 30 ቀን 2006ዓ.ም፣ ዳዎ ወረዳ

## በቀብር ጊዜ

የለቅሶው እድምተኛ በነዚህ ከላይ በተዘረዘሩት የአለቃቀስ ስልቶች ሀዘኑን፣ ፍቅሩን፣ ሲገልፅ ይቆይና እኩለ ቀን ላይ አስክሬን ለቀብር ይነሳል፡፡ በዚህ መሃል ከሩቅ የመጡና ቀብረው በዚያው ይሄዳሉ ተብሎ የሚገመቱ ለቀስተኞች አስክሬን ከመነሳቱ በፊት ለመስተንግዶ በተዘጋጀ ቦታ ምግብ ቀርቦላቸው ይመገባሉ፡፡ አንዳንድ ቦታ ደግሞ የተዘጋጀው ምግብ ቤተክርስቲያን ተውስዶ ከቃብር ሲመለሱ እዚያው እንዲስተናገዱ ይደረጋል፡፡13

በአብዛኞዎቹ በተመለከትኳቸው ለቅሶዎች አስክሬኑ ሲነሳ ከአካባቢው እስኪርቅና ፍጥነት እስኪጨመር ለቀስተኞቹ ቀደም ሲል በተገለፁ የተለያዩ ስልቶች እያለቀሱ አስክሬኑን ያጅባሉ፤ አንዳንድ ቦታ የእምነት አባቶች ተገኝተው በጉዞ ፍታትም የሚሸኙ አሉ(የኦርቶዶክስ ክርስትናውን የሚያጠብቁ ቤተሰቦች)፡፡ በእንደዚህ የአለቃቀስ ስልትና ሁኔታ አስክሬኑ ከቤተክርስቲያን በራፍ ሲደርስ ሦስት ጊዜ አሳልመው ጉድጓድ ወደ ተዘጋጀበት ቦታ ይወሰዳል። በፕሮትስታንት ክርስትና እምነት ተከታዮች ደግሞ የአፈንና የፉከራ አለቃቀስ እምብዛም አይከወንም። ወደ ለቅሶው የሚመጡት ቤተዘመዶች የእምነቱ ተከታይ ካልሆኑ ግን ባህላዊ የአለቃቀስ ዓይነቶቹን ይከውናሉ። የእምነቱ አባቶችም አስፈላጊው ፀሎት ከተደረገ በኋላ ግበዓተ ከመሬቱ ይፈፀማል።

በባህላዊው የለቅሶ አከዋወን መሠረት የሬሳ ሣጥን ከጉድጓዱ እንደ ገባ ለሟች የቅርብ ዘመድ የሆነ ሰው በጉድጓድ ቁፋሮውን ያስጀመረው ሦስት ጊዜ በእጁ አፈር ይረጭበታል፡፡ ሌላው ሰው በአካፋ ይመልስበታል፡፡ ሦስት ጊዜ ማድረጉ በባህሉ አንድን ነገር ለማረጋገጥ፣ ለማስረገጥ ወይም ትክክለኛ ነው ለማለት የሚጠቀሙበት ቁጥር ነው፡፡ ለምሳሌ ሽምግልና የሚቀመጡ ሰዎች ሶስት እንዲሆኑ ይደረጋል ምክንያቱም በአብላጫ ድምፅ ለመዳኘት፣ ምርቃት ሶስት ሰው ይመርቃል፤ ምርቃቱ የተሟላ መሆኑ የሚረጋገጥበት ነው፡፡ በዚያም ጊዜ እንዲሁ በዋይታ ይለቀሳል፡፡ በግበዓተ ከመሬት ጊዜ ማን ምን እንደሚል መረዳት የማይቻልበትና የተደበላለቀ ጩሀትና ዋይታ የሚሰማበት ነው ፡፡ ውተወታ ዓይነት ነው በምልከታ ከተከታተልኩት "Addaanbaane egaa, situ bolltti hafaa, boollatu siin malaa? Itti nafudhukaa....." - "ተለያየን እነግዲህ፣ አንተ/አንቺ ነህ/ነሽ ጉድጓድ የምትቀረው/የምትቀሪው፣ ጉድጓድነው የሚገባህ/የሚገባሽ? ወደ እርሱ ውሰደኛ/ ውሰጅኛ..." የሚሉ ቃላት ይበዛሉ፡፡

## ድህረ ቀብር ሥርዓት

የቀብር ሥነሥርዓት ከተጠናቀቀ በኋላ እዚያው በቤተክርስቲያን የሃይማኖት አባቶች የፀሎትና የማፅናኛ መልእክት አስተላልፈው ፤ የቤተሰብ ምርቃት፣ ምስጋናና መልዕክት ይቀጥላል ፡፡

[13] ጎሮ ወንጪ አካባቢ የተከታተልኩት የአቶ ጎንፋ ኡርጂ ለቅሶ ማስተንግዶ በቤተክርስቲያን ነበር፡፡

**ስለሟች መተረክና ዘመድ የመመረቅ ሥርዓት** (Senaa himuufi Fira Eebbisuu)

ከቤተክርስቲያኑ የማሳረጊያና የማሰናበቻ ሥርዓት በማስከተል ከሟች ቤተሰብ ታለቅ የሚባል ሰው ስለሟች ማንነት ገልፆ በቀብሩ ላይ የተገኘውን ዘመድ አዝማድና አገልግሎት ሲሰጥ የቆየውን ጎረቤትና እድረተኛ እንደሚከተለው ያመሰግናል፣ ይመርቃል ፡፡

ስለሟች ማንነት መግለፅ ሲባል የሟችን የህይወት ዘመን ውሎና ተግባር ለለቅሶው እድምተኞች በይፋ መንገር፣ ማሳወቅ ሲሆን ፣ ልክ በከተሞች የሟች የህይወት ታሪክ በንባብ እንደሚቀርብ በቃል ይነገራል። ከምርቃቱ አስቀድሞ ሟች እንዲህ.... ነበረ/ነበረች እየተባለ ይተረካል፡፡ የ90 ዓመቱ የዕድሜ ባለፀጋ የአቶ ጉርሜሳ ቀብር በተፈፀመ ጊዜ ከቤተሰብ መካከል በዕድሜ ታለቅ የሆኑ ዘመድ እንደሚከተለው ተርከው መረቁ፡፡

> Abbaan keenya nama gaariidha. Namaaf tola, namni rakkadhe jennaan, firri xuqmnaan ciisee hinbulu. Horii namaaf kennee hinfudhatu. Beekaadha, hinbarsiifate, hinfuusise, hinheerumsise. Baddaa gammoojjitti fira nuutolche. Hunda keessummeessee gaggeessa. Abbaa qawwee abbaa minishiriiti. Nuti ilmaan haadha sadiiti. Har'a garuu ilmaan haadha sadii hintaane .Abbaan keenya adaraa ijoollee koo garaa baldhadhaa waliitola. Walitti hinmufatiina tokko yoodabe wajjin hin dabiinaa jedha. Akknatti nuguddifatni.Egaa namni dhalatee du'a hin oolu waggaansaani xinnaa miti har'a waggaa 90 omtuu itti hin hafne.-
>
> አባታችን ጥሩ ሰው ናቸው፣ ደግ ናቸው፣ ሰው ቸገረኝ ካለ፣ ዘመድ ከተነካ ተኝቶ አያድርም፣ ለሰው አበድሮ መልሶ አይወስድም፣ አዋቂ ነው ልጆቹን አስተምሯል፣ ድሯል፣ ከደጋ ከቆላ ዘመድ አበጅቶልና፣ ሁሉንም አስተናግዶ ይሸኛል፡፡ እኛ የሶስት እናት ልጆች ነን፣ ዛሬ ግን እንደ ሦስት እናት ልጆች አይደለንም፡፡ አባታችን ተቻቻሉ፣ አትቀያየሙ፣ አንዱ ቢጣመም አትከተሉት ይላል ፡፡ እንድህ እንደ አንድ እናት ልጆች አሳደጉን፡፡ አባታችን ጀግና ናቸው፣ ባለጠመንጃ፣ ባለምንሽር ናቸው፡፡ ታዲያ ምን ይደረጋል ፤ ሰው ተወልዶ መሞቱ አይቀርም አባታችን ምንም አልቀረባቸውም፡፡ የዘጠና ዓመት የዕድሜ ባለፀጋ ናቸው፡፡

ካሉና የአባታቸውን የህይወት ታሪክ በአጭሩ ከገለፁ በኋላ እንደሚከተለው በቀብሩ ላይ የተገኙትን ዘመድ አዝማድ፣ ጎረቤትና የእድር አባላትን መረቁ ፡፡

| | |
|---|---|
| Firti mana nagaatii baate mana nagaatti gali! | በሰላም ከቤትህ የወጣህ ዘመድ ሁሉ በሰላም ይመልስህ፣ |
| Cufaa banaatti gamadi!<br>Gadda keessa hintaa'iin | በተዘጋውም በተከፈተውም ደስ ይበልህ፣<br>ሀዘን አይድረስብህ፣ |
| Siribaafi mootummaa keessa taa'i… | በደስታ እና በተደላ ውስጥ ኑር |
| Baataan kee hingufatiin, | ፈረስህ አይደናቀፍ፣ |
| Jabbii buraaqxutti gali, | ከሚፈነድቁ ጥጆች/ልጆች ዘንድ ግባ |
| Alangaan siharkaa hin bu'iin | አለንጊያህ/ስልጣንህ ከእጅህ አይውጣ |
| Eebbisee eebbi sittaaqabtu | መርቃለሁ ምርቃቱ ካንተ ይሁን፤ |
| Isaa jannata nuyii sarbii haa kennuu | ለእርሱ ነፍስ ገነት ለእኛ ብረታቱን ይስጥ |
| Warri moodii harka ittin hojjattan kanaa | የእድር አባላት ይህን ሥራ በሠራችሁበት እጅ |
| Foona jabbii ittin ijaarradhaa | የጥጆች ማደሪያ በረት ሥሩ |
| Gateettii ittiin nuubattan kanatti | አስከሬን በተሸከመችሁበት ትከሻችሁ |
| Kumal uffadhaa | ኩታ ደርቡ |
| Nagaa hargadhaa, | ሰላም ይስጣችሁ |
| Qe'ee badhaadheetti galaa | ወደ ታደለ ቄኤ ግቡ |

ብለው ከመረቁ በኋላ "Ollaa qabaa, moodii qaba wajjin gallee buna qammasna" ሟች ጎረቤት እድር አለው አብረን ገብተን ቡና እንቅመስ[14] የሚል መልዕክት አስተላለፉ::

ይህ ሥርዓት ሟች እራሱን አጥፍቶ ከሞተ አይከወንም :: የቀብሩ ሥነሥርዓት እንደተፈፀመ ተስተናግደውና ተሰናብተው መበተን ነው።።[15]

[14] አቶ በዳዳ ሆረሴ ከወሊሶ ወረዳ፣ አቶ ዳበሳ አባመልካ ከወንጪ ወረዳ ቃለመጠየቅ ባደረግሁ ጊዜ ስለቀብር ላይ ምርቃት የገለፁልኝም ይዘቱ ከላይ ከቀረበው ጋር ተመሳሳይ ነው::

[15] ይህንን ዓይነት ሁኔታ የተመለትኩት በጥናቱ አካባቢ አንድ የቤተሰብ አባል የሆኑ ሰው እናት ሞተውባቸው ቀብራቸው ላይ ተገኝቼ ከቀብር በኋላ ስለ ሟች የህይወት ታሪክ ምንም ሳይነገር ምርቃትም ሳይሰጥ ቀባሪው በመበተኑ አዲስ ሆኖብኝ (ሌሎች ቀብሮች ላይ ተገኝቼ ስመለከት በሁሉም ላይ ተከውኗል በቃለመጠቁም ተነግሮኛል) ለምን ምርቃት አንደልተደረገ አንድ ሁለት ሰው ጠይቄ፣ ታንቀው ስለሞቱ ነው የሚል መልስ ተሰጥቶኛል::

### የእንግዳ ማስተናገጃ ድጋፍ ማድረግ (Harka qabachuu)

ከቀብር ሥርዓት በኋላ ዘመድ ሲመረቅ፣ Akka nugonfitanii dhuftanitti manaan nugahaati buna moodiin nuu qophesse waliin dhugnaa"- "እጅባችሁን እንደመጣችሁ እጅባችሁ እቤት አድርሱንና እድራችን ያዘጋጀልንን ቡና አብረን እንቅመስ" የሚለውን መልእክት መሰረት አድርጎ አብሮ ቤት የሚሄድ አለ፤ ይርቀኛል ብሎ መጀመሪያ ላይ ተስተናግዶ ከምርቃቱ በኋላ እዚያው የቀብር ሥነሥርዓት በሚፈፀምበት ቦታ የሚሰናበትም አለ፡፡ ሁሉም ሰው ሲሰናበት እንግዳ አስተናግዱበት በሚል ስሜት ገንዘብ ይሰጣል፡፡ ይህ ገንዘብ እንደ ሰጪው አቅም ትልቅ ትንሽ ሊሆን ይችላል፡፡ ዋና ቁምነገሩ ችግሩ የጋራ መሆኑን ለመግለፅ የሚከወንና የጠለቀ የመተጋገዝ ሥርዓት መኖሩን ለማመልከት የሚደረግ ነው። ገንዘቡን ስጥተው በቃል በቃል ደግሞ "Jabaadha! gaddi sinitti hindeebi'iin" ይላሉ፡፡ ትርጉሙ በርቱ/በርታቱን/ፅናቱን ይስጣችሁ ሀዘን አይመለስባችሁ የሚል ነው፡፡ ይህ የሚባለው ሀሳብ እንደሟቹ ዕድሜና እሟሟቱ ሁኔታ ይለያያል፡፡ የሞተው/የሞተችው ህፃን ከሆነ/ሆነች፣ "jabaadhaa kan guddatu siniif haakennuu" ይባላል፡፡ ትርጉሙ ያፅናችሁ፣ የሚያድገውን ይስጣችሁ ማለት ነው፡፡

### የሀዘን ማብረጃ ሥርዓት (Sirna Bishaan sarbii)

ሀዘንተኞቹ ቤት እንደ ደረሱ የአካባቢው አዛውንት ቆሞ፣ በጮጮ ኪደን ውሃ ብቅል ተጨምሮበት እንዲ ቀርብ አድርጎ "Duuti sitti hindeebi'iin sarbaayi sarbaayi sarbaayi-qabbanaayi" /ሞት አይመለስብህ ቀዝቀዝ በል ብሎ ሀዘንተኞቹ ዓይናቸውን ፊታቸውን እንዲታጠቡበት ያደርጋል፤ ውሃው "Bishaan sarbii" ይባላል፡፡ የማረጋጊያ /የማቀዝቀዣ ወይም የሀዘን ማብረጃ ውሃ ማለት ነው፡፡ ሀዘንተኛው ይህንን ብሻን ሰርቢ ሳይታጠብ ቡና አይቀምስም፡፡ ሀዘንተኞች ቢሻን ሰርቢ ቀርቦላቸው እጃቸውን ታጥበው ፊታቸውን "Waaqi ati sarbii nuu godhi" እያሉ ያብሳሉ፡፡ ትርጉሙ እግዚአብሄር አንተ አብርድልን ማለት ነው[16]

### እንግዳ መሸኘት (Keessummaa Galchuu)

አንድ ሰው ሲሞት በለቅሶውና ቀብሩ ላይ የተገኙ ቀባሪዎች በሁለት መልከ ይስተናገዳሉ፡፡ አንደኛው ከሩቅ የመጡ ቀብር መጠበቅ የማይችሉና ከቀብር በኋለ በዚያው ይሄዳሉ ተብለው የሚገመቱት አስከሬኑ ለቀብር ከመሸኘቱ ቀደም ብሎ ለመስተንግዶ ወደ ተዘጋጀ ቦታ ሄደው እንዲስተናገዱ ይደረጋል፡፡ ተስተናግደው ሀዘንተኛውን ሳይቀበርም ቢሆን ይሰናበታሉ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከቀብር መልስ በሚደረግ የሟች ማንነት ገለፃና ምርቃት ላይ በመጨረሻ

[16] አቶ በቀለ ፉረጋሳ ቃለመጠይቅ ሰኔ 30 ቀን 2006 ከደዎ እና አቶ ዳበሳ አባመልካ ቃለመጠይቅ ሰኔ 26 ቀን 2006፣ ወንጪ ወረዳ፡፡

የተዘጋጀውን ቡና አብረን ገብተን እንቅመስ የሚለውን መልእክት ተቀብለው አስከሬን ወደ ወጣበት ቤት የሄዱትም እንዲሁ በተዘጋጀላቸው ቦታ ሆነው ይስተናገዳሉ፡፡

የመስተንግዶው ዓይነትና ደረጃ እንደ ሟቹና ቤተሰቡ አቅም የተለያየ ይሆናል፡፡ ሟች የእድሜ ባለፀጋ ከሆኑ፣ በኑሮውም የተሻሉ ከሆነ፣ ካላቸው ከብት አንዱ ወይም ከውጭ ተገዝቶ ይታረዳል፣ እህል በሰፊው ቀርቦ ተፈጭቶ ምግብ ይዘጋጃል፣ ቀባሪ በወጉ ይስተናገዳል፡፡ የሌላቸውም ቢሆን እርዱና አረቄው ቢቀር ህዝቡ ባደራጀው እድሩ አማካይነት ቀባሪን ምግብ አብልቶ ቡና አጠጥቶ መሸኘት የግድ ነው ፡፡

እንግዶቹ ከተስተናገዱ በኋላ ለሀዘንተኞቹ ገንዘብ እንደ አቅማቸው እየሰጡ ይሰናበታሉ፡፡ በተመለከትኩዋቸው ለቅሶዎች ሁሉ ይህ ክዋኔ ሲከወን ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ሀዘኑንም ወጪውን መጋራት፣ ጉዳዩ የግል ሳይሆን የጋራ መሆኑንና ያለውን ማህበራዊ ትስስር ያሳያል ፡፡

### የሀዘን ጊዜ ሥርዓት (Sirna yeroo Gaddaa)

ሰው ሞቶ ቀብሩ ከተፈፀመና ቀባሪ እንግዳ ከተሸኘ በኋላ ሞዲ የሚባለው ዕድር የዕለት ተግባሩን ያጠናቅቃል። ጎሎቤ የሚባለው ዕደር ተተክቶ እስከ ሀዘን ማብቂያ ድረስ እንግዳ የማስተናገድና ለሀዘንተኞች አገልግሎት የመስጠት ሥራውን ይያያዛል ፡፡ ምግብ የሚያዘጋጅ፣ ውሃ የሚቀዳ፣ እንጨት የሚያቀርብ፣ ቡና የሚያፈላ፣ ለለቅሶ ከሚመጣው እንግዳ ፈረስ፣ በትር የሚቀበሉና የሚስያተናግዱ ለየብቻ ተመድበው በንቃት ይሰራሉ፡፡ ሀዘን ላይ የሚቆየው ከሦስት እስከ ሰባት ቀን ነው። እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ ለለቅሶ የሚመጡ ሰዎች እንዲያርፉበት ከአጥር ውጭ በር ላይ የተደረደሩ ወንበሮች እዚያው ይቆያሉ ፤ ሀዘንተኞቹም እዚያው ሆነው፣ እያለቀሰ የሚመጣውን እንግዳ አብረው አልቅሰው ይቀበላሉ፡፡ ቤተሰብና የቅርብ ዘመድ ሆነ በአካባቢው የሚገኝ ሁሉ ከሀዘን እስከሚነሱ ድረስ አጅበው እዚያው ይቆያሉ፡፡

ከሦስተኛው ቀን ጀምሮ እስከ ሰባተኛው ቀን “Sirna Iddoo ka’uu” (ከሀዘን ቦታ መነሳት) የሚባል ሥርዓት ይከወናል ፡፡ ሦስተኛው ቀን ከቦታው መነሳት ሳይሆን ትንሽ ፈቀቅ ብሎ እስከ ሰባተኛው ቀን ይቆያል ፡፡ ፈቀቅ ማለት ከአጥር ውጭ የነበሩትን ወንበሮች ወደ ግቢ ገብተው ከቤት ደጃፍ ለይ መደርደርና አልቃሽ እንግዳ እዚያው መቀበል ነው ፡፡ ከሀዘኑ ቦታ ፈቀቅ ካሉ በኋላ እያለቀሰ የሚመጣን ሰው “Qabbaneeffanneerraa dhiisaa” – “ሀዘናችንን አብርደናል በቃ” ብለው ያስቆማሉ ፡፡

ከሀዘን መነሻው ቀን በአብዛኛው ሦስተኛው ቀን ነው፡፡ በሰባት ቀን ነው የሚሉም አሉ፡፡ በወንጪ አካባቢ በሦስተኛ ቀን ከጤፍ ሰባት ቢጢሌ ቂጣዎች ይጋገራሉ፡፡ ትኩስ የታለበ ወተት ይቀርባል (ከቤት ባይኖር እንኳ ከጎረቤት ይጠየቃል) ጫፉ ያልተቆረጠ ሰርዶ ሣር ተነቅሎ ይቀርባል፣ ጫፉ የተቆረጠ ከሆነ ጎዶሎ ስለሆነ መመረቂያ/ሥርዓት መከወኛ አይሆንም፡፡ ቡና ይፈላል፣ በሀዘኑ ላይ ያለ ቤተሰብና ቤተዘመድ ሁሉ ተሰብስቦ መሬት ጅባ ወይም የኮባ ቅጠል ተነጥፎ ክብ ሠርቶ ይቀመጣል፡፡ የተጋገሩት ቢጢሌ ቂጣዎችና ትኩስ ወተቱና ሰርዶ ሣሩ በተሰበሰቡት መሃል

ይደረጋል፤ Guulaa/Abbaa gadaa ወይም ከቤተሰቡ ታላቅ የሆነ ተነስቶ ቆሞ ይመርቃል “Warra kanaaf duuti daari haat’u” “ለነዚህ ቤተሰቦች ሞት ዳር ሁን”ይላል፡፡ በማስከተል ክብ ሰርተው የተቀመጡት አንድ ባንድ ሣሩን ወተቱ ውስጥ በግራ እጃቸው እየነከሩ “Duuti daarii ta’i,duuti daarii ta’i,duuti daarii ta’i” ብለው ተቀበቀብለው ዙሪያው ይዳረሳል ፡፡ ፍችው ሞት ዳር ሁን (ሞት መጨረሻ ሁን) አንድ ሰው ሦስት ጊዜ ሣሩን ከወተቱ እየነከረ ሞት ዳር ሁን እያለ ወደ መሬት እያፈሰሰ ሞትን እየረገመ ተራው ለሁሉም ይደርሳል፡፡ በመጨረሻ የተረፈውን ወተት በየእጃቸው ጨምረው ያለቀሱበት ዓይናቸውን ተቀባብተው፣ ቂጣዎቹም ተቆራርሰው ሁሉም በልተው፣ ቂቤ ቀርቦ ዋና ሀዘንተኛ በተለይ ልጅ እግር የሆነችና ባል የሞታት ወይም ልጅ የሞተባት ከሆነ ይቀቧታል “Qabbanayi”(ቀዝቀዝ በይ) ይሏታል፡፡ ቅቤ የሚቀቧት ሀዘኑ እንዳይከር ነው፡፡ ከከረረ ሌላ ሀዘን ይጨምራል ወይ እርሷንም ይደግማል፤ የሞተባት ልጅ ከሆነ ደግሞ ትደነግጥና መኽን ትሆናለች ተብሎ ስለሚፈራ ነው ለማብረድ ቂቤ የሚቀባው ፡፡ በመረሻ ሁሉም በአንድነት ሞት ዳር ሁን ብለው ይነሳሉ ፡፡

ቅቤ፣ ወተት እና ውሃ የሀዘን ማብረጃ፣ የሰላም፣ የደስታ ምልክት መሆናቸውን ከዋኞቹ ያሳያሉ። ከቀብር ሲመለሱ ቢሻን ሰርቢ ብለው በሰየሙት ውሃ በመጀመሪያ ደረጃ ሀዘናቸውን ያበርዳሉ፡ ከሀዘን በመነሻ እለት በውሃና በወተት ሞት ዳር ሁን አትመለስ ብለው ይሸኙበታል፤ እንዲሁም ሀዘን እንዳይከር፣ እንዳይደግም ሀዘንተኛን ቅቤ ይቀባሉ፡፡ እነዚህ የሀዘን ማብረጃዎች በዚህ አውድ ደረጃ በደረጃ አጋልግሎት የሰጡ ተምሳሌት ገላጭ ቁሶች ናቸው፡፡

በዳዎ ወረዳ ደግሞ ከሀዘን በሚነሱ ቀን ጉላ/አባገዳ ወይም ሽማግሌ (ሥርዓቱን አስፈፃሚ አባት) መጥቶ፤ ሁለት ቂጣ ይጋገራል፡፡ አንዱን ቂጣ የሞተው ወንድ ከሆነ ለወንድ ውሻ፣ የሞተችው ሴት ከሆነች ደግሞ ለሴት ውሻ ይሰጣል፤ ውሃም በሁለት ዕቃ ይቀርባል፡፡ በአንደኛው ዕቃ ውስጥ ካለው ውሃ በሣር እየነከሩ ዓይናቸውን ይታጠባሉ “Lammata simboochisiin” (ሁለተኛ አያስለቅስህ/ሽ) እየተባለ፣ በሁለተኛው ዕቃ የቀረበውን ውሃ በግራ እግሩ ረጭቶ (አባገዳው) “Duuti badi,lammata asitti hindeebi’iin” (ሞት ጥፋ! ሁለተኛ እዚህ እንዳትመለስ) ይላል፡፡ ውሃውን በግራ እግር መድፋት ሞትን ግራ ሁን አይቅናህ ማለት ሲሆን ውሃው ደግሞ ሞትን ውሃ ሁን ጥንካሬ አይኑርህ፣ ድከም ማለት ነው፡፡ አንዳንድ ቦታ ላይ በእግር የሚደፋውን ውሃ ትንባሆ የተጨሰበት Bishaan Gaayyaa -የጋያ ውሃ የሚያደርጉ አሉ ፡፡ ይህም ሞትን እንደ ትንባሆው ውሃ ግማ/ተጠላ/ተወገዝ ብለው ይረግማሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ሦስት ቦታ ላይ ቁጥጥ ቁጥጥ ብለው ተቀምጠው መጀመሪያ ወደ ነበሩበት ቦታ ተመልሰው ይቀመጣሉ፡፡ ይህ ደግሞ ሀዘኑ አብቅቶ ወደ መደበኛ የዕለት ተዕለት ኑሮአቸው መመለሳቸውን ለማመልከት የሚደረግ ነው። ሁለተኛው ቂጣ ተቆራርሶ እዚያ ለነበሩት ሁሉ እንዲዳረስ ተደርጎ ይበላሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ከሀዘን ተነስተዋል የትም መሄድ፣ ሥራቸውን መስራት ይችላሉ።17

[17] አቶ በቀለ ፉፋ ቃለመጠይቅ ሰኔ 26 ቀን 2006 ዓ.ም ዳዎ ወረዳ ፡፡

በወሊሶ ወረዳም18 እንዲሁ በሦስተኛው ቀን ሀዘንተኞቹ ከነበሩበት ውጭ አጥር በር አካባቢ ፈቀቅ ብለው "Biddeena Nagaa tolfatanii" (የሰላም እንጀራ) የተባለ ጋግረው በልተው፣ ቡና አፍልተው ጠጥተው ከሀዘን ይነሳሉ ፡፡ በዚህ ሥርዓት ላይ የሚከተለው ተግባር ይከወናል ፡፡

> Awwaalanii torbanitti biddeena nagaa tolfatanii buna danfifatanii eebbisu, Yawaaqi nagaa nuugodhi,nagaa ta'aa,kan du'e hingalu,walii obsaa,warri jiraattan waliin jiraadhaa,waliin nyaadhaa kunoo kanuma arginu kana akkanumatti badu,boru haadhufuu iftaan haadhufuu wanti beekamu hinjiru,waljaaldhaa,jaalala sinii haakennu,si'achi sintu dhaqa malee kan du'e hingalu.Uffata gurracha kana hin uffatiinaa yoo dhiisan rabbis namaa dhiisa jedhanii eebbisanii akka qabbana'u godhu.፡-ቀብሩ ተፈፅሞ በሦስተኛው የሰላም እንጀራ ጋግረው ቡና አፍልተው ይመረቃል እግዚአብሔር ሰላም አድርግልን፣ ሰላም ሁኑ፣ የሞተ ሰው አይመለስም/አይገባም፣ ተፅናኑ፤ በህይወት ያላችሁ አብራችሁ ኑሩ፣ አብራችሁ ብሉ፣ ይኸው የምናየው ነው ሞት ነገ ይምጣ ተነገወዲያ ይምጣ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ ተዋደዱ ፍቅር ይስጣችሁ፡፡ ከዚህ በኋላ እናንተ ትሄዱ እንደ ሆነ እንጂ የሞተ አይመለስም፡፡ ይህን ጥቁር ልብስም አትልበሱ፣ ከተዉ/ካቀዘቀዙ አምላክም ይምራል።

ብለው መርቀው ሀዘኑ እንዲበርድ ያደርጋሉ። ሰው ሲሞት የቤተሰብ አባለት ሁሉ ጥቁር ልብስ፣ የነበረን ጥቁር ወይም ሰማያዊ ቀለም በመንከር፣ ወንዶች ጥቁር ጥለት (ቱቢት ) የተመታበት ነጠላ በመልበስ፣ ኮታቸው ላይም ጥቁር ጥለት(ቱቢት) አሰፍተው ጥቁር ኮፊያ እራሳቸው ላይ አድርገው ፅማቸውን ባለመላጨት ሀዘንተኛነታቸውን ይገልፃሉ፡፡ ሴቶችም እንዲሁ ጥቁር ልብስ አሰፍተው፣ ያለቸውን ቀለም ነክረው ወይም ጥቁር ጥለት (ቱቢት)አስመትተውበት፣ ፀጉራቸውን ተላጭተው ወይም በጥቁር ሻሽ አስረው ቅባትና ቅቤ ከመቀባት ታቅበው በሀዘን ላይ ይቆያሉ፡፡ ይህን የሀዘን ልብስ ለብሰው የሚቆዩበትን ጊዜ የሚችና የሀዘንተኞቹ የሥጋ ዝምድና ቅርበት እና የመዋደድ ደረጃ ይወስነዋል፡፡ ሦስት ወር፣ ስድስት ወር ሀዘን ልብስ የሚለብሱ አሉ፡፡ ሶስትና ስድስት በባህሉ የወቅትና የእኩለ ዓመት መለኪያ ነው፡፡ ስለዚህ በትንሹ እሩብ ዓመት ማዘን የተለመደ መሆኑን ለመግለፅ የሚጠቀሙበት ነው፡፡ የሀዘን ቆይታው እንደሰው ባህሪም ይለያያል፤ የሚያከሩ በተለይ ሴቶች ባልና የደረሰ/የደረሰች ልጅ የሞተባቸው ዓመትና ከዚያም በላይ የሚቆዩና አባቶች ተቆጥተው የሚያስጥሉዋቸው አሉ፡፡ "ድሮ ድሮማ በሀዘን ጊዜ ሰውነታቸውን የማይታጠቡ፣ ጥፍራቸውን የማይቆርጡ ነበሩ፣ አሁን ቀለል ብሏል መተዛዘኑም ይህን ያህል አይደለም በተለይ በተለያዩ እምነቶች መስፋፋት ምክንያት ባህላዊ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔዎች እየተተዉ፣ አዘቅዝቆ መልበስ እንኳ እየቀረ ነው።"19 አለመታጠቡ ጥፍር አለመቁረጡ አራስን በመጣልና በመነሳቀል

[19] አቶ በዳዳ ሆርሴ፣ አቶ አስፋው ከወሊሶ ወረዳ አቶ ዳበሳ አባመልካ ከወንጪ ወረዳ ቃለመጠይቅ ፡፡

ምን ያህል ሀዘን እንደተሰማቸው ለማሳየት፣ እንዲሁም ማማር ከሟች ጋር ቀረ ለማለት የሚያደርጉት ነበር፡፡

## ሟች የማስታወስ ሥርዓት (Sirna Hordaa Buqqisii)

የሀዘን አደጋ ያጋጠመው ቤተሰብ ሟችን የሚያስታውስባቸው ሥርዓቶች አሉ፡፡ አንዱ በመንፈስ ሟችን በማሰብ የሚበላና የሚጠጣ አዘጋጅቶ ምርቃት የሚሰጥበት Hordaa Buqqisii የተባለው ነው፡፡ ሆረዳ ቡቂሲ ጥሬ ትርጉሙ መቆፈሪያ ነቀላ ማለት ነው ፡፡ ሟች ከተቀበረበት ዕለት ጀምሮ የሆርዳ ቡቂሲ ሥርዓት እስከ ሚከወንበት ድረስ በመቆፈሪያ ተወግቶ እንዳለ ስለሚታሰብ ሥርዓቱ ተከውኖ የሟች መንፈስ አያት ቅድመ አያቶቹ እንዲደመር ይደረጋል ፡፡

ሌላው የሟች ማስታወሻ በባህሉ ሰው ሲሞት በቀብሩ ላይ ምልክት (ሃውልት፣ ቤት በመሥራት ወይም የተተለያዩ ተክሎች እንዲበቅሉ) በማድረግ የቀብር ቦታው እንዳይረሳ ሟቹም እንዲታወስ ይደረጋል ፡፡

ለሟች ማስታወሻ የሚሆን ነገር ማቆምና ሰፊ ዝግጅት ማድረግ እንደ ቤተሰቡ አቅም ይለያያል፡፡ አቅም ያለው እንደ ከተማው ሃውልት አሰርቶ ያስታውስበታል፡፡ አልቻልም ያለው ደግሞ በቀብሩ ላይ አነስተኛ ቤት ያሰራበታል፣ በዚህ አጋጣሚ ለቀሪ ቤተሰብ እንዲሆን ሰፋ አድርጎ የሚሰራም ይኖራል፡፡ ለዚህም የሚሆን የለኝም ያለ ቀብሩ በተፈፀመ በወሩ በቀብሩ ላይ ለምልሞ የሚቆይ ተክል ይተከላል፡፡ ከብትም ታርዶ፣ ጠላ ተጠምቆ፣ ዘመድና ጎረቤት ተጠርቶ ኦረዳ ቡቂሲ (የማስታወሻ ሥነሥርዓት) ይፈፀማል፡፡

በየዓመቱ በቤት ባህላዊ ምግብ(ዳቦ)ና መጠጥ(Farsoo Oromoo) አዘጋጅተው ጎረቤት ጠርተው Saqdada baasu- ተዝካር ማውጣት፣ ቀኑን በማሰብ ያከብራሉ፡፡ አፈፃፀሙ፣ "Guulli dhaabbatee Jennanni abbaa/haadha kootii irraa gadeen sitiksaa jalaa olee natikisi, sa'a naaqajeelchi,nama naaqajeelchi waan hundaa naaqajeelch jechisisee eebbisa" ይህም ማለት ሥርዓቱ የተዘጋጀበት ቤት ጉላ (አባገዳ) ተጠርቶ መጥቶ ተዝካር የሚያወጣውን ሰው "የአባቴ/እናቴ መንፈስ ወደ ታች እጠብቅሃለሁ ከታች ወደላይ ጠብቀኝ፣ ከብቱን አስተካክልልኝ፣ ሰውንም አስተካክልልኝ፣ ሁሉንም ነገር አስተካክልልኝ በል" ብሎ እንዲመረቅ ያደርጋል፡፡ ከላይ ወደ ታች እጠብቅሃለሁ አንተ ከታች ወደላይ ጠብቀኝ የሚለው አባባል የሞተ ሰው መንፈስ ከምድር በታች እንደሆነ እን በህይወት ያለው ደግሞ ከምድር ላይ ሆኖ እንደሚጠባበቁ ስለሚታሰብ የሚባል አባባል ነው፡፡ከተመረቀ በኋላ ዳቦው ተቆራርሶ ጠላው ቀርቦ በሥርዓቱ ላይ ለተገኘ ሁሉ ተሰጥቶ በልተው ጠጥተው "Akknumtti waggaa waggaadhaan abbaa kee/hadhakee si haa yaadachiisu ayyanni abbaa kee/haadha kee si haatikisu እንዲሁ በየዓመቱ አበትህን/እናትህን አስታዋሽ ያድርግህ የአባትህ/እናትህ መንፈስ ይጠብቅህ" ብለው መርቀው ይሰናበታሉ፡፡ ይህ በየዓመቱ የሚዘጋጀው የወላጆች ማስታወሻ ሥርዓት "Saqadada Basuu" ይባላል፡፡ የሟች ልጆች በህይወት እስካሉበት ጊዜ ድረስ በየዓመቱ ይከበራል፡፡ ይህ ደርጊት ልጅ እስካለ የሚቀጥል ሲሆን የሞተ ስለማይመለስ እንደ

ማስታወሻ ተጠቅመው ሟችን የሚያስቡበት ነው፡፡ የአካባቢው ኦሮሞ "Ijibbaanni du'aa saqadada baasuudha" ይላል፡፡ ማለትም የሞት መጨረሻው የማስታወሻውን ሥርዓት መከወን ነው/ተዘካር ማውጣት ነው፡፡ ከዚህም ሌላ በአካባቢው በክርስትና ሃይማኖት ደንብ መሰረት ከአርባ ቀን መታሰቢያ ጀምረው ሙት ዓመት የማውጣት ሥርዓት የሚከተሉ በብዛት እንዳሉ መረጃዎቹ ያረጋግጣሉ፡፡

## የሟች ንብረት የማስተላለፍ ሥርዓት (Sirna Dhaalaa)

ንብረት የሚያስተዳድር አባት ሲሞት በድሮው ወንድም በውርስ (ጋብቻ ፈፅሞ) ልጆቹና፣ ንብረቱ ለባዕድ ሳይጋለጥ ይተዳደራሉ የሚለውን አስተሳሰብ በማራመድ ንብረት የማስተዳደር ሥርዓት ነበር፡፡ መረጃዎቹ እንደሚያሳዩት ይህን አሰራር ማስቀጠል የሚፈልጉ አልፎ አልፎ የሚታዩ ቢሆኑም በአሁኑ ጊዜ ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ ህጎች ንብረቱን ልጆችና ለሚስት እንደከፋፈሉ ስለሚያዙ በዚያ መሠረት ይሠራል ፡፡

አከፋፈሉ ቤተሰባዊ ሽማግሌ ተቀምጦ በባህላዊ ህግ መሠረት ታላቅ ወንድ ልጅ የአባቱ ወንበር፣ ኮርቻ እና ጦር የመሳሰሉትን ሌላው ሳይጋራው እንዲወስድና የተቀረውን ንብረት በሙሉ እኩል እንዲካፋፈሉ ያደርጋል። ይህ ንብረት የማካፈሉ ሥርዓት ድሮ ለወንዶች ብቻ ነበር፤ በአሁኑ ጊዜ ግን አግብተው በትዳር ያሉ ሴቶች ሳይቀሩ ከወንዶች እኩል የአባታቸውን ንብረት እንደሚካፈሉ መረጃዎቹ ያረጋግጣሉ።

## ሞት የሚያስከትላቸው ተፅዕኖዎች

ከንብረት መከፋፈል አስቀድሞ መታየት ያለበት ጉዳይ የሞት አደጋ የደረሰበት ማነው የሚለው ነው፡፡ ሞቱ የደረሰው በቤተሰብ መሪ ወይም ጧሪ ላይ ከሆነ የመተዳደሪያ አቅም ጥያቄ ውስጥ ይገባል፡፡ በተለይ የደረሰ ወንድ ልጅ የሌለበት ቤተሰብ ችግራቸው እጥፍ ድርብ ይሆናል ፡፡ ጠምዶ የሚያርስ ያስፈልጋል ፡፡ አጭዶ መከመር፣ መውቃት የመሳሰሉትም እንዲሁ በአባወራው፣ በደረሱ ወንዶች ልጆች የሚሰሩ ናቸው፡፡ ለማሰራት ገንዘብ ወይም እገዛ የሚያደርግ የቅርብ ሰው ያስፈልጋል፡፡ ከቤት ውጭ ያለ የአደባባይ ጉዳይ እንዲሁ በባህሉ የወንድ ተሳትፎ የሚፈልግ ይሆንና የሟችን ቤተሰብ ጥገኛ፣ ችግረኛና ከማህበራዊ ኑሮ የራቁ የሚያደርጉ ይሆናል፡፡

ያልደረሱ ልጆች ያሉዋት እናት ብትሞትም እንዲሁ ለአባወራው አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ልጅ ማሳደጉ፣ አብስሎ ማቅረቡ የሴቷ ድርሻ በሆነበት ባህል የቤተሰቡ እጣፈንታ መበተን ይሆናል፡፡ አንዳንድ በቅርበት የተመለከትኳቸው ለቅሶዎች እናቶች የሞቱበት ሲለቀስ "ልጆችሽን ለማን አደራ ሰጠሽ፣ ቤትሽ ተዘጋ" የሚሉ ናቸው፡፡ "ህፃናት ልጆች ነበሯት ሰውየው ብቻውን ምን ያደርጋል እህቶች ተከፋፈሉ" እየተባሉ የሚተላለፉ ሀሳቦች በየሀዘን ቤቱ ሲተረክ በምልከታ ጊዜ ማደመጥ ተችሏል። እንዲህ አይነት አደጋ ያጋጠመው ቤተሰብ ውስጥ በእገዛ ወይም በቅጥር አብራ የምትኖር ሌላ ተንከባካቢ ሴት ከሌለች ከመከፋፈል የተሸለ አፋጣኝ መፍትሔ ላይኖር ይችላል፡፡

ሌላ ሚስት ያግባ ቢባል ሌላ ችግር መጨመር ሊሆን ይችላል፤ ጊዜም ይፈልጋል።በአጭር ጊዜ ውስጥ ማግባት ባህሉም አይፈቅድም ፡፡

## የሞትና የሀዘን ሥርዓቱ ትንተና

የሞትና ሀዘን ሥርዓት ከህይወት ዑደት የመጨረሻው ሲሆን ቫን ጄኔፕ የህይወት ዑደቶች በገለፀባቸው የመለየት፣ የሽግግር እና የመቀላቀል የሥርዓት ደረጃዎች ውስጥ ያልፋል፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የቀረቡት የሞትና የሀዘን ሥርዓቶች መረጃዎች እንደሚያመለክቱት አንድ ሰው በጠና ታሞ አልጋላይ ከዋለ ጊዜ ጀምሮ ለየት ተብሎ ይታያል፡፡ ታሞ ሰርቶ መግባት ሲያቅተው፣ ለምግቡ፣ ለጤናው እንክብካቤ የሰው እጅ መጠበቅ ሲጀምር ከጤናማዎቹ ይለያል፡፡ በህይወት ባሉ ጤናማ እና በሞቱት መካከል ሆኖ በፀሎት፣ በህክምና እጣ ፈንታውን እየጠበቀ ከዳነ ወደ ቀድሞው ህይወቱ ይመለሳል፡፡ ብሶበት ከሞተ ደግሞ ህይወት ካላቸው ተለይቶ ሙት/በድን ይሆናል፡፡ ታሞ እንክብካቤ ሲደረግለት ቆይቶ ሲሞት ሁለት ዓይነት የመለየት ደረጃዎችን ያልፋል ማለት ነው፡፡ የሟች ቤተሰቦችም ከመደበኛ ውሎአቸው ተለይተው ቤት ይውላሉ በስሜት ደግሞ ሀዘንተኛ ይሆናሉ፡፡ ይህንን ከተገለፁት የለቅሶ ሥርዓቶች ጋር አያይዘን ብንመለከት ታማሚው ሰው ፀንቶበት ነፍስ ከሥጋው ስትለይ ለማስተካከል የተቀመጡት ይገንዛሉ፡፡ እጅ እግሩ ጣቶች ታስረው በህወት የነበረው ሰው ህይወት አልባ በድን ሆኖ በህይወት ካሉት ይለያል፡፡ ከቀድሞ በተለየ ይፈራል፣ በህይወት ካሉት ከቤተሰቡ፣ ከዘመድ አዝማዱ ከወገኑ ከጎረቤቱ በመለየቱ ከያሉበት ተጠራርተው በህብረት፣ ያለቅሱለታል ያዝኑለታል፡፡

አስከሬኑ ተቀብሮ የመሰናበቻና የማሰታወሻ/መዘከሪያ ሥርዓት እስከሚዘጋጅለት ድረስ ሟችም ሆነ ቤተሰቡ በሽግግር ደረጃ ውስጥ ይቆያሉ፡፡ ከቀብር ተመልሰው ሀዘኑ እንዲበርድ ዓይናቸውን “በብሻን ሰርቢ” አብሰው ሀዘናቸውን አብርደው፣ ከየዘመዱ የእንግዳ መሸኛ ተቀብለው እንግዶቻቸው ተስተናግደው ተሸኝተው፣ ከሦስት እስከ ሰባተኛው ቀን የሞቱን መርዶ እየሰሙ ከሚመጡ ዘመድ አዝመዘድና ወዳጅ ጋር እየተላቀሱ ቆይተው “biddeena nagaa tolfatni ,duuti daarii ta’i” የሰላም ህብስት/ዳቦ ጋግረው ሣር ወተት እየነከሩ ሞት ዳር ሁን፣ በግራ እግር ውሃ ወይም የትንባሆ ውሃ ደፍተው ሞትን ግራ ሁን፣ ውሃ ሁን፣ ድከም፣ ተጠላ ብለው ረግመው ከሀዘን ቦታ ይነሳሉ፡፡ መደበኛ የእለት ተግባራቸውን መከወን ቢጀምሩም በሀዘን ውስጥ ይቆያሉ ፡፡

የሟች ወገኖች ወር ቆይተው “horda buqqisii” -ዶማ ነቀላ ሥርዓት አዘጋጅተው ዘመድ አዝማድ ጠርተው ሟችን አስታውሰውና ለመጫረሻ ጊዜ ተሰናብተው ሀዘን እንዳያፀኑ ተመክረው ለሟች ላዘጋጁት ማስታወሻ ይመረቃሉ፡፡ በዚሁ ሂደት ሟች ቀድሞ ከሞቱት ወገኖቹ ጎራ ይደመራል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ሀዘንተኞች ለሟች ካላቸው ቅርበት የተነሳ ሀዘናቸውን ለወራትና ለዓመት ሊቀጥሉ ይችላሉ፡፡ ግን በሆርዳ ቡቅሲ ሥርዓት ከማህረሰቡ ጋር ተመልሶ መቀላቀልና ወደ ቀድሞው የእለት ተእለት የህይወት እንቅስቃሴዎቻቸው መመለስ ይጀምራሉ። እንዚህ በየደረጃው የሚከወኑ የሀዘን ሥርዓቶች የቤተሰቡን የየዘመዱን አብሮነት፣ ፍቅርና አንድነት መተሳሰብ አመልካቾች ናቸው።

በአጠቃላይ የህይወት ዑደት የሰው ልጅ የሚያልፍባቸውን ዋናዋና ተፈጥሮአዊና ማህበራዊ የህይወት እርከኖች ማሳያ ነው። የህይወት ዑደት የህይወት ውጣ ውረድ፣ ደስታና ሀዘን የሚፈራረቁበት፣ ጉዳዮች ከግለሰብ ተነስተው ወደ ማህበረሰብ እየሰፉ የሚሄዱበት ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ የህይወት ዑደቶቹ ደረጃቸው ይለያይ እንጂ ከግላዊ ይበልጥ ማህበራዊ መዋቅራቸው እየሰፋ የሚሄድ ነው።

ከላይ እንደቀረበው በሞት ሥርዓትም በህይወት የነበረ ሞቶ ኢያት ቅድመ ኢያት የሚሆንበት ሂደት ላይ ለመድረስ ታሞ ከቤተሰቡ፣ ከቤተዘመዱ፣ ከጎረቤቱ እጅ ወድቆ ሲታገዝ ቆይቶ ሲሞት ዘመድ አዝማዱ፣ ወገኑ፣ ጓደኞቹ፣ እድርተኞቹ ተጠራርተው አልቅሰው፣ አዝነው አስተዛዝነው፣ ማስታወሻ አቁመውለት እስከሚሰናበቱት ጉዳዩ ከራሱና ከቤተሰቡ አልፎ የአካባቢው ነዋሪና የጎሳው የወገኑ ሆኖ ለመሰባሰብ፣ ለመጠያየቅ ለመተጋገዝና ለመረዳዳት ሰበብ ይሆናል።ሞት ከቤተሰብ፣ ከጎረቤት፣ ከወገን ከጎሳ አባላትን ለዘላለም በመነጠል የሚያለያይ፣ በሟች ይረዳ የነበረን ቤተሰብና ወገን ረጂ ነስቶ የሚያጎል ቢሆንም በጎደለው ወገናቸው ሸኝትና ስንብት ምክንያት መሰባሰብ፣እንደገና ግንኙነትን ለማጠናከር ቃል የሚገባቡበት በመሆኑ የአብሮነት ስሜትም የሚታደስበት ነው።

ወሊሶ ሊበንም ሞትን መግቢያ ውስጥ እንደ ቀረበው በሶስት ከፍሎ ደረጃ ቢሰጠውና አንዱ ከሌላው ይሻላል ቢለውም ሞት በህይወት የነበረን ሰው ከቤተሰብ፣ ከዘመድ አዝማድ፣ ከጎረቤትና ከሀገር የሚለይ ማስቀረት የማይቻልና የሚረገም መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል፡፡ በተጨማሪም በጥናቱ መረጃዎች ውስጥ የተንፀባረቁት የፎክሎር ዓይነቶችና ተምሳሌታዊ ክዋኔዎች ህዝቡ ማንነቱን፣ አብሮነቱን ጠብቆ እንዲቆይ ያደረጉ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፉ የቆዩት የህዝቡ እውቀቶችና ባህላዊ እሴቶች ተሸካሚዎች እንደሆኑ ጥናቱ አሳይቷል።

በዚህ ጥናት ለመጠቃቀስ እንደተሞከረው በሞት ምክንያት የሚከወኑ ሥርዓቶችና የሚያጅቡ ክዋኔዎች በርካታና ጥልቅ ናቸው፡፡ በመሆኑም ለወደፊት ከፍልስፍና፣ ከስነልቡና እና ከሃይማኖት አንፃር በዝርዝር ቢጠና ህዝቡ ለህይወት የሚሰጠውን ቦታና ለማህበራዊ መስተጋብር ያለውን አተያይ ማሳየት ይቻላል የሚል አሰተያየት አለኝ፡፡

## References


Alembi, E. (2001). *The Abanyole Dirge: "Escorting" the Dead with Song and Dance*. Retrieved 9 20, 2013, from www.folklore.ee/folklore.

Alembi, E. (2002). *The Construction of the Abanyole Perceptions on Death Through Oral Funeral Poetry*. Filand: University of Helsinki.

Cederroth, S. C. (1988). *On the Meaning of Death:Essays on Mortaury Rituals and Ecological Beliefs* . Sweden.

Dorson, R. M. (1972). *Folklore and Folklife: An Introduction.* Chicago: The University of Chicago Press.

Fetterman, D. M. (2010). *Ethnography:Step-by-Step (third ed.)* . New Delhi: Sage Publication,Inc.

Geertz, C. (1973). *The Interpretation of Culture:Sellected Essays.* New York: Basic Book Publishes Inc.

Halifax, S. G. (1977). *The Human Encounter With Death* . New York: Sequoia-Elsevier Publishing Co.

Hill, J. & Daniels, P. (2008). *Life Events and Rites Passage.* USA: Omngraphics.

Kaufman, S. R. (2005). *The Anthropology of the Beginning and Ends of Life.* Annual Review of Antropology, 317-341.

Palgi, P. & Abramovitch, H. (1984). *Death: A Cross-Cultural Perspective.* Annual Review of Anthropology, Vol. 13, pp. 385-417.

Sims, Martha C. & Stephens, Martine. (2005). *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions.* Logan, Utah: Utah State University Press.

Calilasseia, ADParker (2013) biologically speaking, what is Death? http://www.rationalskepticism.org